**ወቅታዊ ጉዳይ**

# አላህ የሚለው ስምና የቁርዓን መጽሐፍ ታሪካዊ አመጣጣቸው ሲፈተሽ

አፈወርቅ ዘአትናቴዎስ

ባለፉት ተከታታይ ዓመታት የእስልምና ሃይማኖት እናስተምራለን ባዮች ቁርዓናቸውን መተርጐም ትተው መጽሐፍ ቅዱሳን አብዝተው በመተቸት ደከሙ:: ለአብነትም ያህል የሚከተሉትን መጥቀስ ይቻላል:: በዶ/ር ማኅሕ ሐምማድ አልጀህይኒ የተዘጋጀው «ነቢ ኢየሱስ እውነተኛ መረጃ» ተከታታይ ዕትም ቁጥር ፱ ገጽ ፳፱ ላይ ትምህርተ ሥላሴን ዕንቆቅልሽ ፈጠራና የበላይነት ለመያዝ የሚታገሉ ሰዎች ፍልሚያ ይሉታል:: ሱለይ ማን ሙፊሰር የተባሉ ሰውም «ኢየሱስ በቁርዓን» በሚለው መጽሐፋቸው ገጽ ፯ ላይ ይህንኑ ትምህርተ ሥላሴን «የአሳዋቂነት መርሆ» ይሉታል:: አብዱልመሊክ ዓል አልኩለይብ እንደ ደረሱትና መሐመድ ኢብራሒም እንደ ተረጐሙት በሚገልጸው «የፈጣሪ አንድነት በኦሪት፣ በወን ጌልና በቁርዓን» የሚለው መጽሐፍ ገጽ ፮ ላይ ደግሞ «ኢየሱስ የአላህ ነቢይ ቢሆንም ክርስቲያኖች ሃይማኖቱን አዛቡት፣ ከውስጡም ብዙ ቀየሩት...» በማለት ጽፈዋል:: ይህን ስናይ ለመሆኑ ሃይማኖትን ያዛባው ማን ነው? በርግጥ እኛን ተሳስተዋል ብለው ለሚያስቡት ለእነዚህ ሰዎች እኛ ብንደክ ምላቸው የሚገባን አይደለምን? በማለት አሰብን:: ትንሽ ቆይተን ደግሞ ቀመር ሁሴን ያዘጋጁትን «የመጽሐፍ ቅዱስ ምስጢር በሙስሊም መነጽር» መጽሐፉ ውስጥ ገጹ ፫ ላይ መጽሐፍ የተዘጋጀበት ዓላማ «ክርስቲያኖችን ተውራትን አምጡና አንብቡት፤ እንወያይ እውነተኛ ከሆናችሁ በሏቸው» ለማለት መጻፋቸውን ስንመለከት ለመወያየትማ ከፈቀዱ ውይይቱ በመጽሐፍ ቅዱስ ብቻ ሳይሆን በቁርዓንም ጭምር መሆን እንዳለበት አሰብን:: እኚሁ ሰው «ስህተትን መመለስ» በሚል ርእስ በጻፉት ላይ ደግሞ ጌታችን ብቻ ሳይሆን ቅዱስ ጳዉሎስንም በስድብ ይወርፋሉ:: ከዚህም በኋላ «መጽሐፍ ቅዱስ ስለ መሐመድ የተናገረው ቃል» የሚለውን በአሕመድ ሁሴን ዲዳት ተጽፎ በዘካሪያ አባትሁን ወርቅነህ የተተረጐመውን ስንመለከት የውይይቱን አስፈላጊነት ከበቂ በላይ ተረዳነው:: «ኢየሱስ ፈጣሪ ነውን?» የሚለው የዚሁ የአሕመድ ዲዳት ሌላ መጽሐፍ ደግሞ የበለጠ ለመልስ የሚጋብዝ ሆኖ አገኘ ነው:: ነጃሺ አሣታሚ ድርጅት ያሳተመው ይህ መጽሐፍ እጅግ በድፍረት፣ የተሞላና በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ፌዝ መሰል ነገሮችን አንግቦ መነሣቱን ስናይ በርግጥም ለወንድሞቻችን በትምህርት ልንደርስላቸው ስለ ቁርዓንና ስለይዘቱም በምሁራን የተጠኑትን አገላብጠን የተሰወረውን ልንገልጥላቸው አስፈላጊ ሆኖ አገኘ ነው:: «አንዳንዶቻችን ተከራካሪዎቻችንም ውቀሱ፣ አንዳንዶቻችንም ከእሳት ነጥቃችሁ አድኑ» ተብለን ታዝዘናልና:: ይሁ. ፩÷፳፫ በዚህ ሁኔታ እንዳለን ግን ሁኔታዎች በፍጥነት ተለወጡ:: በዚህ አላቆሙም:: የክርስቲያኖችን ሕይወት በቤተ መቅደስ እስከ ማጥፋት ተደረሰ:: ከዚህም በላይ በካሴቶችና አሁንም በተለያዩ መጻሕፍት ብዙ የሚያደናግሩ ነገሮችን በማውጣታቸው ብዙ ክርስቲያን ወንድሞቻችንና እኅቶቻችን ታወኩ:: በተለይ በቅርቡ ከአዲስ አበባ ራቅ ባሉና ክርስቲያኖቹ ባነሱባቸው አካባቢዎች ያሉ ወንድሞቻችን ላይ ያለባቸው ተጽእኖ እየጨመረ መጥቷል:: አንዳንዶቹ በግልጽ «የማታስተምሩንና እውነቱን የማትነግሩን ከሆነ ከእነርሱ ያላነሠ በደል እንደፈጸማችሁብን ዕወቁት» እያሉ አሳዛኝ መልእክቶቻቸውን በስልኮቻችን ያስደምጡናል:: አንዳንዶቹ መጥታችሁ እንኳ ባታስተምሩን ባላችሁበት ሁናችሁ የምናስተምርበት ጽሑፍ እንኳ ለምን አታዘጋጁልንም? ይላሉ:: በጣም የተሰማቸውም «የአዲስ አበባ ሊቃውንት ስለ ክርስቶስ የሚመሰክሩት መቼ ነው? እርሱ እኮ ለእኛ ነው መስክሩ ያላችሁ፣ እናንተ ግን መልሳችሁ ለራሱ ለጌታ መንገር የምትፈልጉ ይመስላል፤ እናንተ መጽሔትና ጋዜጣ የምታዘጋጁትስ ብትሆኑ በእስልምና ላሉት ወንድሞቻችን ያዘጋጃችሁት የፍቅር ብዕራችሁ የት አለ? ለጥያቄያችን የምትሰጡት መልስስ ምንድን ነው? ለእኛስ ራሳችንን የምናጸናበት ትምህርታዊ ጽሑፎችን ካላ ደረሳችሁ የመኖራችሁ ጥቅሙ ምንድን ነው?» እያሉ ይወቅሱናል:: እነዚህንና ሌሎችንም ጥያቄዎች ግምት ውስጥ በማስገባት መጽሐፍ ቅዱስን ብቻ ከማስተማር እንደ እነርሱ ሁሉ ስለቁ ርዓን ማስተማር አስፈላጊ መሆኑ ብቻ ሳይሆን ጊዜ ሳንሰጥ መሥራት የሚገባን እንደሆነ እየተረዳን መጣን:: በዚህም መሠረት ስለ እስልምና፣ መሐመድና ቁርአን እርስ በእርሱ የሚጋጭ ስለመሆኑ የተለያዩ ተመራማሪዎች የሠሯቸውን ሥራዎች በማገናዘብ የመጀመሪያውን ሥራችን እነሆ ብለናችኋል:: የጠፋውን ለማዳን የመጣው መድኅኔዓለም ክርስቶስ ለባዘኑት መገኘትን፣ ለጠፉት መዳንን፣ ያድልልን ዘንድ በመመኘት ወደ ጽሑፉ እናመራለን::

# የእግዚአብሔር ስምና «አላህ» የሚለው ስም የትመጣ

## ፩. አላህ የእግዚአብሔር ስም ነውን?

በእስልምና ሃይማኖት የአምላካቸው ስም አላህ ነው። ይህ ስም ምንጩ ከየት ነው? በእርግጥስ እነርሱ (እስላሞች) እንደሚሉት ይህ ስም በፊት፤ በብሉይ ኪዳን ኋላም በሐዲስ ኪዳን የተገለጸው አምላክ ስም ነው? ክርስቲያኖችና እስላሞችስ አምላካቸው አንድ ነው? ልዩነት ካለስ የስም ልዩነት ብቻ ነው ወይስ መሠረታዊ የሆነ የ<ምን>ነትና የ<ምን>ነት ልዩነት አለ?

## ፪. የእግዚአብሔር ስም በመጽሐፍ ቅዱስ ወስጥ

ብሉይ ኪዳንን የሰጠው አምላክ ስሙ ያህዌ (YHWH) ነው። ይህም «ዘሀሎ ወይሄሉ - ያለና የሚኖር» ማለት ነው። ዘፍ.፫፥፲፬። ምንጩም ሀዋህ - መኖር ከሚለው የዕብራይስጥ ቃል ነው። በእስላሞች መጽሐፍ የአምላካቸው ስም አላህ እንደሆነ ሁሉ፤ መጽሐፍ ቅዱስ ላይ የተገለጸው አምላክ - የእግዚአብሔር ስም ደግሞ ያሕዌ ነው። ዋናው መሠረታዊ ነገር ያህዌ የሚለው ስም ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጭ ማንንም ሌላ አምላክ ለማመልከት ወይም ለመግለጽ ውሎ የማያውቅ መሆኑ ነው። እግዚአብሔር ራሱን ከመግለጡ በፊት ከዕብራውያን በስተቀር ያሕዌን ያመልክ የነበረ ነገድም ሆነ ሃይማኖት አልነበረም። ስለዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ስም «ያህዌ» ለመጽሐፍ ቅዱስና ለሚያምኑበት ብቻ የተለየ ስም ነው። ያህዌ የሚለው ስም ከሌላ ባህልም ሆነ እምነት ያልተወረሰ ወይም ያልተቀዳ፣ ሌላ አሕዛባዊ ምንጭ የሌለው ነው። የተገለጠው በራሱ በመጽሐፍ ቅዱስ መገለጥ ነው።

አላህ የመጽሐፍ ቅዱስ አምላክ እንደሆነና በቅዱሳት መጻሕፍትም ውስጥ እንደተጠቀሰ እስላሞች ይናገራሉ። ይህ ደረቅ ስሕተት ነው። አላህ የሚለው ስም በብሉይ ኪዳንም ሆነ በሐዲስ ኪዳን አንድ ጊዜም እንኳ የተጠቀሰበት ቦታ የለም። እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳን በስም የተገለጸው ያህዌ (ማለትም ዘሀሎ ወይሄሉ - ያለና የሚኖር) በሚል ነው። «ጀሆቫህ» የሚለው ስም የእግዚአብሔር መጽሐፍ ቅዱሳዊ ስም አይደለም። ያህዌ የሚለውን ቅዱስና ገናና ስሙን መጥራት የፈሩ አይሁድ የፈጠሩት መጥሪያ ስም እንጂ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቃል ወይም ስም አይደለም።

## ፫. አላህ የሚለው ስም የትመጣ

እንደ ጥንት ታሪክ ጥናት ማስረጃዎች «አላህ» በመካ ይመለኩ ከነበሩት ብዙ ጣዖታት መካከል ዋና ነው ተብሎ ይታመን የነበረው «አምላክ» ስም ነበር። «አላህ» የሚለው ስም አል እና ኢላህ (al" and "ilah") ከሚሉት የዐረብኛ ቃላት የተገኘ ቃል ሲሆን አምላክ (የታወቀ አምላክን ወይም ጣዖትን - "the god" or "the idol.") የሚገልጽ ነው። እስላም ማለት ለአላህ መገዛት፣ ራስን መስጠት ማለት ሲሆን በመጀመሪያ (በጥንት) ትርጉሙ ግን በአስቸጋሪ ሁኔታዎች እንኳ ለራሱ ጎሳ ሲል እስከ ሞት ድረስ ጸንቶ የሚዋጋ የበረሃ ጦረኛ ጥንካሬና ድፍረት ማለት ነበር። (Dr. M. Baravmann, *The Spiritual Background of Early Islam*, E. J. Brill, Leiden, 1972) አንዳንዶች አላህ የሚለው ቃል «ኤል» ከሚለውና በከነዓናውያንና በዕብራውያን እውነተኛም ይሁን ሐሰተኛ አምላክን ከሚያመለክተው ቃል የተገኘ እንደሆነ ያምናሉ። ነገር ግን ይህ አይደለም። ታዲያ የዚህ ቃል ምንጭ ምንድነው?

አላህ የሚለው ቃል ከዐረብኛ የተገኘ ቃል ነው። ይህም የሚያሳየው ከዚያው ከዐረብኛ የተገኘ እንጂ በዕብራይስጥና በግሪክ ከተጻፈው መጽሐፍ ቅዱስ ያልተገኘና ምንም ዓይነት ዝምድና የሌለው መሆኑን ነው። አላህ ሙሉ በሙሉ ዐረቦች ያመልኩት የነበረውን አምላክ ለመግለጽ ይጠቀሙበት የነበረና ዐረብኛ ብቻ የሆነ ቃል ነው። ዕብራዊ ምንጭ የለውም። የሃይማኖት መድበለ ዕውቀት መጽሐፍ «አላህ ከባቢሎናውያን አምላክ ከቤል

ጋር የሚመሳሰል ... ከእስልምና በፊት የነበረ ስም ነው» ይላል:: (The *Encyclopedia of Religion*: ed. James Hastings, Edinburgh, T. & T. Clark, 1908, I:326).

ይህን በሌሎች በብዙ ማስረጃዎች ማየት ይቻላል::

- «አላህ ከእስልምና በፊት በነበሩ የዐረብኛ ጽሑፎች ላይ ይገኛል» (*Encyclopedia Britannica*, I:643)
- ዐረቦች ከመሐመድ መነሣት በፊት በነበሩት ዘመናት አላህ የሚባል ሉዐላዊ አምላክ ያመልኩ ነበር:: (*Encyclopedia of Islam*, eds. Houtsma, Arnold, Basset, Hartman; Leiden: E.J.Brill, 1913, I:302)
- «አላህ ከእስልምና በፊት በነበሩት ዐረቦች ይታወቅ ነበር ... እርሱም ከመካ አማልክት አንዱ ነበር:: (*Encyclopedia of Islam*, ed. Gibb, I:406)
- «ኢላህ የሚለው ቃል ቅድመ እስልምና በነበሩ ድርሰቶች ይገኛል ... ተደጋግሞ ጥቅም ላይ ሲውል አል-ኢላህ የሚለው ቃል አላህ በሚለው ቃል እየተተካ መጣ:: ይህም በቅድመ እስልምና ታሪክ ተደጋግሞ የሚገኝ ነው::(*Encyclopedia of Islam*, eds. Lewis, Menage, Pellat, Schacht; Leiden: E.J.Brill, 1971, III:1093)
- «አላህ የሚለው ስም ከመሐመድ በፊት የሚቀድም ስም ነው::» (*Encyclopedia of World Mythology and Legend*, "The Facts on File", ed. Anthony Mercatante, New York, 1983, I:41)
- «አላህ ለዐረቦች በስሙ አስቀድሞ ይታወቅ የነበረ ነው:: (*The Bible and Islam: or, the Influence of the Old and New Testament on the Religion of Mohammed*, New York: Charles Scribner's Sons, 1897, p.102)
- «አላህ የሚለው ስም ከእስልምና በፊት በነበረው የዐረቢያ የከርስ ምድር ጥናት ውጤቶችና በሥነ ጽሑፍ ቅሬቶች በግልፅ የሚገኝ ስም ነው::» (*The Call of the Minaret*, New York: OUP, 1956, p.31)

አላህ የሚለው ስም በቅድመ እስልምና ዘመን የታወቀና የነበረ የመሆን ጉዳይና በነ በረው ዕንስ አሳብ ላይ የብዙ ዘመን ጥልቅ ምርምርና ጥናት ያደረገ ሞንትጎሜሪ (ዶ/ር) የተባለ አንድ ተመራማሪ ጥናቱን እንዲህ በማለት አጠቃሏል:-

*«እየተረዳሁት የመጣሁት ነገር ቢኖር፤ የመሐመድን ተግባርና የእስልምናን ምንጭ በበቂ ሁኔታ ለመረዳት በመካ እንደ ከፍተኛ አምላክ ይመለክ የነበረ «አላህ» የሚባል አምላክ የነበረ የመሆኑ ጉዳይ ከፍተኛ ትኩረትና ዋጋ ሊሰጠው የሚገባ መሆኑን ነው:: ይህ የጣዖት አምልኮ ዓይነት ነው፤ ሆኖም ግን በተለምዶ ከሚታወቀው የጣዖት አምልኮ የተለየ በመሆኑ ልዩ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል::»* (*Mohammad's Mecca*, p.vii. , "Belief in a High God in pre-Islamic Mecca", *Journal of Scientific Semitic Studies*, vol.16, 1971, pp.35-40)

አላህ የሚለው ስም ቅድመ እስልምና በነበረው ትርጉም ላይ ሰፋ ያለ ጥናት ያደረገው ፋራህ የተባለ ተመራማሪም ጥናቱን እንዲህ በማለት ይደመድማል:-

*«ስለዚህ አላህ የሚለው ስም ለእስላሞች ከክርስቲያኖችና ከአይሁዶች የተላለፈላቸው (የወረሱት) ነው የሚለውን የእስላሞችን አስተሳሰብ ለመቀበል ምንም ዓይነት ምክንያት የለም»* (*Islam: Beliefs and Observations*, New York: Barrons, 1987, p.28)

የቁርአን ትርጉሙ አሁን ድረስ በአገልግሎት ላይ የሚገኘው የመካከለኛው ምሥራቅ ጥናት ሊቅ የሆነው ኤ. ም. ዌሪ «በቅድመ እስልምና ዘመን የአላህ አምልኮ እና የበኣል አምልኮ ፀሐይን፣ ጨረቃን እና ከዋክብትን የሚመለከቱ በሰማይ ካሉ ሥነ ፍጥረታት ጋር የተያያዙ አምልኮዎች ነበሩ» ይላል:: (*A Comprehensive Commentary on the Quran*, Osnabrück: Otto Zeller Verlag, 1973, p.36).

«በጥንታዊ ዐረቦች የፀሐይ አምላክ እንደ ሴት አምላክ ትታይ የነበረ ሲሆን፤ የጨረቃ አምላክ ደግሞ እንደ ወንድ አምላክ ይታይ ነበር:: በብዙ ሊቃውንት ጥናት እንደተመለከተው የጨረቃው አምላክ በተለያዩ ስያሜዎች ይታወቅ ነበር:: ከእነዚህም አንዱ አላህ ነበር:: (op.cit., *Islam*, p.7)

«አላህ የሚለው ስም የጨረቃ አምላክ የግል መጠሪያ ስሙ ነበር:: ... የጨረቃው አምላክ - አላህ - ከፀሐይዋ አምላክ ጋር ተጋባ:: ሁለቱ በአንድነትም «የአላህ (ሴት) ልጆች» የተባሉ ሦስት አማልክትን አስገኙ:: እነዚህ ሦስት አማልክትም አል-ላት፣ አል-ኡዛ እና አል-ማናት ይባሉ ነበር:: የአላህ ልጆች ከአላህ ጋርና ከፀሐይ አምላክ ጋር እንደ «ከፍተኛ» አምላክ ይታዩ ነበር:: ማለትም እነዚህ ብዙ ከሆኑት ከሁሉም የዐረቦች አማልክት የመጀመሪያው ተርታ ላይ ያሉ ተደርገው ይታዩ ነበር:: (**Robert Morey, *The Islamic Invasion*, Eugene, Oregon, Harvest House Publishers, 1977, pp.50-51).**

ከእስልምና መምጣት በፊት ዐረቦች ብዙ ወንድና ሴት አማልክትን ያመልኩ ነበር፤ እያ ንዳንዱ ጎሳም የራሱ «አምላክ» ነበረው:: በዛን ዘመን «አላህ» የሚታወቀው የጨረቃ አምላክ ተብሎ የነበረ ሲሆን፤ ሕዝቡን ከአላህ ጋር የሚያማልዱ ናቸው ተብለው ይታመኑ የነበሩ ሦስት ልጆች ነበሩት:: ስማቸውም አል-ላት፣ አል-ኡዛ እና አል-ማናት ነበር:: የመጀመሪያዎቹ የሁለቱ ስም የአላህ የሴት አንቀፅ የሆነ ስም ነው:: በመካና አካባቢዋ የዐረብ ምድር ከ፫፻፷ አማ ልክት በላይ (በዓመቱ ቀናት መጠን) ነበሩ:: (*Encyclopedia of Religion and Ethics* (ed. Hastings), I:326.)

«ሆኖም ከአላህ ጋር ሌሎች ትናንሽ አማልክትንና የ«አላህን ልጆች» ያመልኩ ነበር:: (**The *Encyclopedia of World Mythology and Legend*, I:61)**

ከእስልምና መምጣት በፊት የጨረቃ ምስል በዐረብ ምድርና በመካከለኛው ምሥራቅ የጨረቃ አምላክ (አላህ) አምልኮ ምልክት ነበር:: የአማልክት ምስሎችና ቅርፆች በሆኑ ሀውልቶችና ጽሑፎች ላይ የጨረቃ ምስሎች እና ቅርፆች በብዛት ተገኝተዋል:: ሁለት እጆቹ የጨረቃ ምስል ወደ ሆነ ቅርጽ እንደሚጸልይ ሆነው የተዘረጉ የጥቁር ድንጋይ ሐውልት በፍልስጥኤም ተገኝቷል:: እስራኤላውያን እውነተኛውን አምላክ እግዚአብሔርን እንዳያ መልኩ ይፈታተኗቸው የነበሩት በአካባቢው አሕዛብ ተስፋፍተው የነበሩት የፀሐይ፣ የጨረቃና የከዋክብት አምልኮዎች ነበሩ:: ዘዳ.፬÷፲፱፤ ኤር. ፯÷፲፰፤ አሞ.፭÷፳፮፤ የሐዋ.፯÷፵፫::

አል-ላት የምትወከለው አራት ማዕዘን በሆነ ድንጋይ ሲሆን ዋና መቅደሷ የነበረውም በጣይፍ ከተማ ነበር:: በመቅደሱ ውስጥም በመካና በመዲና መካከል በቁዳይድ ከተማ ላይ ጥቁር ድንጋይ ነበር:: እርሷም የዕድል አምላክ ስትሆን የአላህ አንስታይ ተነፃፃሪ ነበረች:: አል-ኡዛ ደግሞ የምሥራቃዊ መካ አምላክ ነበረች::

አላህ የሚለው ስም ራሱ ቁርአን እንደሚመሰክረው ከእስልምና መምጣት በፊት በዐረቢያ ምድር ይታወቅ ነበር:: አላህ የሚለው ስም፣ እንዲሁም አነስታይ ተነፃፃሪው አል-ላት የሚለው ስምም በሰሜን አፍሪቃና በዐረቢያ ምድር በሚገኙ የድንጋይና የመሬት ላይ ጽሑፎች ላይ ተደ ጋግመው ይገኛሉ:: (Arthur Jeffrey, ed., *Islam: Muhammad and His Religion* (1958), p. 85.)

በዐረብ ምድር የጨረቃ አምላክ ዋናው እምነት እንደነበር የከርሰ ምድር ቅርሶች ታሪክ ጥናት በሚገባ ያሳያል:: ብሉይ ኪዳን በተደጋጋሚ የጨረቃን የጣዖት አምልኮ ይነቅፍና ያስጠነቅቅ ነበር:: ዘዳ.፬÷፲፱፣ ፲፯÷፫፣፤ ፪ነገ.፳፩÷፫÷፭፤ ፳፫÷፭፤ ኤር.፰÷፪፤ ፲፱÷፲፫፤ ሶፎ.፩÷፭:: እስራኤላውያን በጣዖት አምልኮ ሲጠመዱ ብዙውን ጊዜ በጨረቃ ጣዖት ነበር:: በብሉይ ኪዳን ዘመን ናኒዶስ (፭፻፶፭-፭፻፴፱ ቅ.ል.ክ) የተባለ የባቢሎን ንጉሥ ዐረቢያን የጨረቃ አምልኮ ማዕከል አደረጋት:: በሌሎች ሕዝቦች ዘንድ የጨረቃ አምልኮ እየቀነሰ ሲሄድ፤ ጨረቃ ከሁሉም በላይ ናት የሚለው እምነት በዐረቦች ዘንድ የጸና ሆኖ ቆየ:: መካ ውስጥ ፫፻፷ አማልክትን ሲያመልኩ የጨረቃን አምላክ የእነዚህ ሁሉ የበላይ አድርገው ያመልኩ ነበር:: መካ የተሠራችው የጨረቃ አምላክ ልዩ መቅደስ ሆና ነበር:: መካን የዐረብ ምድር የጣዖት አምልኮ «የተቀደሰች ቦታ» እና መነኻሪያ ያደረጋትም ይኸው ነበር::

የታሪክ ምሁራን እንደሚገልጹት መሐመድ በተነሣ ጊዜ በዐረቢያ ምድር ይመለኩ የነበሩት የ፫፻፷ዎቹ አማልክት የበላያቸው ወይም ዋናቸው ተደርጎ የሚታመነው አላህ ነበር:: ሆኖም ብዙ እስላሞች «አላህ» በመካና በዐረብ ምድር ከመሐመድ መምጣት በፊት በዐረቦች ይመለክ እንደነበር መስማትም ማወቅም አይፈልጉም::(G. J. O. Moshay, *Who Is This Allah?* (Dorchester House, Bucks, UK, 1994), pg. 138).

መካ እና «ቅዱስ ድንጋይ» አል-ካባ ከእስልምና በፊት ለነበሩት ጣዖት አምላኪ የዐረብ ጎሳዎች አምልኮና የቅድስና ቦታዎች ነበሩ:: በመካ ያለው ካባ የቀድሞ ስሙ «ቤት አላህ» ማለትም የአላህ ቤት ነበር:: ይህም መጀመሪያ በሰማይ የተሠራና የዚያ ምሳሌና አርአያ እንደሆነ ይነገራል:: ይህም ሙሴ እንዲሠራ ከታዘዘውና በመጽሐፍ ቅዱስ ከተነገረው የተኮረጀ ነው:: ዘጸ. ፳፭÷፱::

መሐመድ ሌሎች ጣዖታትን እንዳጠፋና በአንድ አምላክ ማመንን እንዳስተማረ፣ እርሱም የእርሱ መልእክተኛ መሆኑን ቁርዓን ይነግረናል:: ካባ የተቀደሰና ልዩ ቦታ መሆኑን፣ እንዲሁም በዚያ ያለው ጥቁር ድንጋይ የሰዎችን ኃጢአት የማስተሥረይ ኃይል እንዳለው ይገልፃል:: ማንኛውንም አማኝ በሕይወት ዘመኑ ቢያንስ አንድ ጊዜ ወደዚህ ድንጋይ እንዲሄድ ያስገድዳል:: ከብሉይ ኪዳን አባቶችና ነቢያት ወደ መካ የሄደ፣ ካባን ሄዶ ጥቁሩን ድንጋይ የሳመ ማንም የሌለ ሲሆን ነገር ግን አብርሃምና እስማኤል እንደሠሩት ይተረካል:: (ሱራ፳፪÷፳፮-፴፯)

መሐመድ ቀድሞ የአንድ ጣዖት ስም የነበረውን «አላህ» የሚለውን ስም፤ የመካ ሰዎች ያመልኩት ከነበረው አላህ በምን እንደሚለይ ሳይገልጽ እንዳለ የአንዱ «ብቸኛ አምላክ» ስም አደረገው:: ይህ የቀድሞ አምልኮታቸውን የማደስ እንጂ ሙሉ በሙሉ የመለወጥ አልነበረም:: ሕዝቡን ስሕተታቸውን (የቀድሞውን፣ ጣዖቱን) አላህ ትተው ትክክለኛውንና አዲሱን፣ ብቸኛ የተባለውን አላህ እንዲያመልኩ አላላቸውም::

መሐመድ የተወለደበት የቋሪሽ ነገድ አላህ ከሚባለው የጨረቃ አምላክ ጋር ከፍተኛ የሆነ ቁርኝትና ለእርሱም ከፍ ያለ አምልኮ ነበራቸው:: በተለይም ደግሞ በሕዝቡና በአላህ መካከል አማላጆች ናቸው ተብለው ለሚታመኑት ለሦስቱ የአላህ ልጆች::

የመሐመድ የአባቱ ስም አብደ-አላህ (የአላህ አገልጋይ፣ ባሪያ ማለት ነው) ነበር:: የአጎቱ ስም ደግሞ ኦብየድ አላህ ነበር:: እነዚህ ስሞች የሚያሳዩት የመሐመድ ቤተሰቦች ለአላህ የነበራቸውን አምልኮና አላህ የሚለው ስም በእርሱ ቤተሰብ ዘንድ በሚገባ ይታወቅ የነበረ መሆኑን ነው:: እንዲሁም በመሐመድ ብቸኛ (አንድ) አምላክ ከመደረጉ በፊት በነበረው የብዙ አማልክት አምልኮ ውስጥ አላህ የሚለው ስም የነበረ መሆኑን በግልጽ ያሳየናል:: አላህ የሚለውን ስም የተጠቀሙት ጣዖት አምላኪዎች የነበሩ መሆናቸውን ልብ አድርግ:: (op.cit., Morey, p.51). በመሐመድ ነገድ የጨረቃን አምላክ ስም በግለሰብ የመጠሪያ ስምነት መጠቀም የተለመደ እንደነበር አይተናል:: ስለዚህ አላህ ቅድመ እስልምና የነበረ የጣዖት አምላክ መሆኑ ሊስተባበል የማይችል ሀቅ ነው:: የመሐመድ አምላክ ለምን የእርሱ ነገድ አምላክ፤ በነበረ የጣዖት አምላክ ስም ተሰየመ? ብለን ራሳችንን እንድንጠይቅ ያደርገናል::


የጨረቃ አምልኮ በዐረቢያ ምድርና በአካባቢው የተስፋፋ ነበር:: ይህም ጥንቱንም የጨረቃን አምላክ -አላህ- ያመልኩና የጨረቃን ምስል የአምልኮታቸው መገለጫ ያደርጉ በነበሩ ሕዝቦች ዘንድ፤ እስልምና ያገኘውን ተቀባይነትና በቀላሉ መስፋፋት ለመረዳት ያስችላል:: እንዲሁም ጨረቃ ለምን የእስልምና ምልክትና ዓርማ ተደርጎ እንደተወሰደም ለመረዳት ይረዳል:: ይህ ሁሉ አላህ በመካ እንደ ጨረቃ አምላክ ይመለክ ወደነበረበት ከዛሬ ብዙ ዓመታት ወደኋላ የሚወስድ ነገር ነው::

እስላሞች አላህ የሚለው ስም የትመጣ ወይም ምንጭ መጽሐፍ ቅዱስ መሆኑን ለማሳመን ለምን ይጨነቃሉ? ከዚህስ ምን ያገኛሉ? አላህ የሚለው ስም ከመጽሐፍ ቅዱስ የተገኘ መሆኑን ማሳመን ከቻሉ ከአይሁዳዊነት ወደ ክርስትና ከዚያም ወደ እስልምና ሽግግር ተደርጓል ለሚሉት ዋና መሠረታዊ የመከራከሪያ አሳብ አስረጅ ይሆነናል ብለው ስለሚያምኑ ነው:: አይሁዶችንና ክርስቲያኖችን ወደ እስልምና ለመለወጥ መንገዱን ቁልቁለት ያደርግልናል ብለው ስለሚያስቡ ነው:: አላህ የሚለው ስም አንዱ አምላክ በቅዱሳት መጻሕፍት አማካይነት ራሱን የገለጠበት ቀጣይ ሂደት ከሆነ እስልምና ከመጽሐፍ ቅዱስ ቀጥሎ የሚመጣ እምነት መሆኑ ነው:: ይህም ማለት አይሁዳዊነት በክርስትና እንደተተካ፣ ክርስትናም በእስልምና ተተካ ማለት ነው:: ነገር ግን አላህ የሚለው ስም ከመጽሐፍ ቅዱስ ምንም ፍንጭ የሌለው እና ከእስልምና መምጣት በፊት በዐረብ ምድር

የነበረ የጣዖት «አምላክ» ስም ከነበረ ደግሞ የእስልምና መሠረት ፋርሽ ሆነ ማለት ነው። ለዚህ ነው አላህ የሚለው ስም የጨረቃ አምላክ ስም የነበረ፣ ከጣዖት አምልኮ የተወረሰ መሆኑን ከላይ ሰፋ አድርገን ማየት ያስፈለገን።

በዐረቢያ ምድር የተገኙ የተለያዩ የከርሰ ምድር ቁፋሮ ውጤቶች አላህ የተባለው አምላክ የጣዖት አምላኪዎች «አምላክ» የነበረ መሆኑን በግልጽ ያሳያሉ። ከፀሐይ አምላክ ጋር የተጋባና ሦስት ልጆችን ያስገኘ «አምላክ» ተብሎ ይታመን እንደነበር በብዙ ማስ ረጃ ዎች የተመሰከረ መሆኑን አይተናል። ከቱርክ ተራራዎች እስከ ግብጽ ድረስ ተ ስፋፍቶ የነበረው የጣዖት አምልኮ የጨረቃ አምልኮ ነበር። በሥነ ፍጥረት ተመራምሮ ወደ ፈጣሪው እስኪደርስና እግዚአብሔርም ተገልጦ አገሩንና ቤተሰቦቹን ሁሉ ትቶ ከከለዳውያን ዑር እንዲወጣና ወደ ከነዓን እንዲሄድ እስኪነግረው ድረስ የአብርሃምም እምነት ይኸው ነበር።


ለምሳሌ ያህልም ከመሬት ቁፋሮ የተገኙና የዛን ዘመን የመካከለኛውን ምሥራቅ የአምልኮ ሁኔታዎችንና ሥርዓቶችን የሚያሳዩ ግኝቶችን ፎቶ የተወሰኑትን ከዚህ በታች መመልከት ይቻላል።




*በቱርክ የተገኘ የግድግዳ ላይ ሥዕል - የጨረቃና የኮከብ ቅርፅ መኖሩን አስተውል*



*ሌላ ቅድመ እስልምና ጨረቃና ኮከብ ከተመሳሳይ ቦታ ላይ*




ቅድመ እስልምናና ዘመነ እስልምና የጨረቃና የኮከብ ቅርፆች
የአናቶሊያ(ግራ)፣ እስላማዊ(መካከለኛ)፣ ጥንታዊ የፋርስ የጨረቃ አምላክ (ሴት) (ቀኝ)



ካራን በጨረቃ አምልኮ የታወቀች ነበረች።
ከላይ ያለው የባቢሎናዊያን የጨረቃ
አምላክ ምስል ነው። የጨረቃ ምስል
መኖሩን አስተውል።

አላህ ይባል
የነበረው ጣዖት
ሦስቱ ልጆች፡ -
አል-ላት፣ አል-ኡዛ
እና
አል-ማናት ከአላህ
ጋር



ይህ እውነት መሐመድ «አላህ» የሚለውን ስም በቁርዓን ለምን እንዳልተረጎመው ያስረዳናል:: መሐመድ ለዐረቦች ስለ አላህ ሲናገር፣ ከዚያ በፊት ምንም ሰምተውት ለማያ ውቁ ሰዎች አዲስ አምላክ እንደሚናገርና እንደሚያስተዋውቅ ሳይሆን አላህ ማን እንደ ሆነ አስቀድሞ ለሚያውቅ ሰው እንደሚናገር ባለ ሰው አቀራረብና አነጋገር ነው የተናገ ራቸው:: አላህን የማያውቁትና አዲስ አምላክ እያስተዋወቃቸው ቢሆን ኖሮ፣ አላህ እን ዲህ ነው በማለት ማንነቱን ማስተማር ከሁሉም በፊት ይቀድም ነበር:: መሐመድ በአላህ አምልኮ ያደገ ነው:: ነገር ግን ከሌሎቹ ፓጋን ዐረቦች አንድ እርምጃ አልፎ ሄደ:: እነርሱ የጨረቃ አምላክ የሆነው አላህ ከሌሎቹ አማልክት የበለጠና ቀዳሚው ነው ብለው ሲያ ምኑ፣ መሐመድ ግን አላህ ከሁሉም አማልክት የሚበልጠው ብቻ ሳይሆን ብቸኛውም አምላክ ነው አለ::

መሐመድ በተግባር ያለው እንዲህ ነው:- «የጨረቃን አምላክ አላህን ከሁሉም አማል ክት በላይ መሆኑን ከበፊትም ጀምሮ ታምናላችሁ:: አሁን እኔ ከእናንተ የምፈልገው ነገር ቢኖር እርሱ ከሁሉም የሚበልጥ ብቻ ሳይሆን ብቸኛ አምላክ መሆኑን ነው:: ቀድሞም የምታመልኩትን አላህን አልወሰድባችሁም፤ ሌላ የማታውቁት እንግዳ አምላክም አላመጣባችሁም:: እኔ ያስወገድኩት ሚስቱን (የፀሐይን አምላክ)፣ ልጆቹን እና ሌሎቹን አማልክት በሙሉ ነው::»

ይህም ከመጀመሪያው የእስልምና የሃይማኖት መግለጫ - አላህ ከሁሉ የበለጠ ነው - ከሚለው ግልፅ ሆኖ ይታያል:: «አላህ ታላቅ ነው» ("Allah is great") - ሳይሆን ንጽጽ ርን በሚያሣይ ሁኔታ «አላህ (ከሁሉም) የበለጠ ነው» ("Allah is the greatest") ነው የሚል:: ይህም ማለት ከሌሎቹ አማልክት የበለጠ ነው ማለት ነው:: ይህም በመሆኑ ፓጋን (ጣዖት አምላኪ) የነበሩት ዐረቦች አስቀድሞም ያውቁት ከነበረውና ከሚያ መልኩት አምላክ ውጭ ሌላ አዲስ አምላክ እንዳመጣባቸው አድርገው አልተናገሩትም፣ አልተጣሉትምም፤ «አላህ ማነው?» ብለውም አልጠየቁትም:: «ከዚህ በፊት የማናውቀ ውን አዲስ አምላክ ከየት አመጣኸው?» አላሉትም:: አላህ የሚለው ስም ለእነርሱ እንግዳ አልነበረምና:: ሲያመልኩት የነበረ የሚያውቁት ነው::

ስለዚህ መሐመድ በሁለቱም በኩል አትራፊ የሆነ ስልትን ለመጠቀም ሞከረ:: ለጣዖት አምላኪ ፓጋኖች አሁንም በጨረቃ አምላክ በአላህ አምናለሁ አላቸው:: ለአይ ሁድና ለክርስቲያኖች ደግሞ አላህ የእነርሱም አምላክ ነው ለማለት ሞከረ:: ነገር ግን በባሕሪው ያለና የሚኖር - ያሕዌ - ዘላለማዊ አምላክን የሚያመልኩ ክርስቲያኖችና በኋላ ተስ ፋውን ባለመቀበላቸው ራሳቸውን ከድኅነት ውጭ ያደረጉ አይሁድም ሁለቱም የመሐመድ የጨረቃ አምላክ - ሐሰተኛ አምላክ - መሆኑን ስለሚያዉቁ ውድቅ አደርገውበታል:: የቀደሙ የክርስቲያንና የእስላም ክርክሮችን በጥልቀት ያጠናው ኒውማን (ዶ/ር) ጥናቱን «እስላም ከጣዖት አምልኮ የተወለደ፣ የተለየና በጥላቻ የታመቀ እምነት ነው» በማለት ጥናቱን አጠ ቃሏል:: (Three Easly Christian-Muslim Debates, ed. by N.A.Newman, Hatfield, PA, IBRI, 1994, p.719)

እስላሞች ይህን ሁሉ የክርስቲያኖች የጥላቻ መግለጫ ነው ብለው ያስቡ ይሆን? ታዲያ የእስልምና ምልክት ጨረቃ መሆኗ በአጋጣሚ የመጣ ይሆን? የጨረቃ ምስል በመስጊዶ ቻቸውና በሚናሬቶቻቸው ጫፍ ላይ መቀመጡ እንዲሁ ያለ ምንም ታሪካዊ የት መጣ የተደረገ ይሆን? የጨረቃ ምልክት በብዙዎቹ እስላም አገሮች ባንዲራ ላይ መደረጉስ? ጨረቃ በሰማይ ላይ መታየት ስትጀምር በሚጀምረው ወር ጀምረው ይህቺው ጨረቃ ስትታይ በሚ ያልቀው ወር የሚጾሙትስ?

## ፬. ከእስልምና በፊት የነበሩ ጣዖታዊ ልምዶች

የጥንት ፓጋን ዐረቦች እምነታቸውን የሚፈጽሙባቸው የአምልኮ መግለጫ ተግባራት ነበሯቸው:: ከእነዚህም የሚከተሉት ዋናዎቹ ነበሩ::

፩. ወደ መካ ዞሮ በቀን አምስት ጊዜ መጸለይ፣

፪. ወደ መካ ጉዞ ማድረግ፣

፫. በካባ (ቤት አላህ - የአላህ ቤት) ዙሪያ መሮጥና መዞር፣

፬. ጥቁሯን ድንጋይ መሳም፣
፭. ለጨረቃ አምላክ የእንስሳ መሥዋዕት አርዶ ማቅረብ፣
፮. በዲያብሎስ ላይ ድንጋይ መወርወር፣
፯. ጨረቃ መታየት ጀምሮ እንደገና ስትታይ በሚያልቀው ወር መጾም፣
፰. ለድሆች ምጽዋት በመስጠትና የመሳሰሉትን በማድረግ ነበር፡፡

እነዚህ ሁሉ የጥንት የፓጋን ዐረቦች የአምልኮ መግለጫዎች ዛሬም በእስልምና ውስጥ ዋናዎቹ የእምነት ተግባራት ናቸው፡፡ ታዲያ እስልምና ከጥንቱ የጣዖት አምልኮ የሚለየው ምንድን ነው?

እስላሞች አንድ «አምላክ» - አላህን ብቻ ማምለካቸው የሚያመልኩት አምላክ እውነተኛው አምላክ መሆኑን አያረጋግጥልንም፡፡ ተመሳሳይ ጣዖታዊ ተሐድሶ በጥንት ዘመናት ይደረግ ነበር፡፡ ለምሳሌም በጥንታዊ ግብጽ፤ ፈርዖን አኬናቶን፣ የፀሐይን አምላክ አቶንን ብቸኛው አምላክ በማድረግ፣ የሌሎች አማልክትን አምልኮ ሕገ ወጥ በማድረግ፤ ሌሎች አማልክትን ሲያመልኩ የተገኙትንም በማሰቃየትና በማጥፋት፤ «አንድ አምላክ አምላኪ - monotheist» ለመሆን ወስኖ ነበር፡፡ እዚህ ላይ ከእስልምና ጋር ተነጻጻሪ የሆኑ ሦስት ነገሮች አሉ፡፡ አንደኛ፣ አኪናቶን ለእነርሱ ወንድ የሚሉትን የፀሐይን አምላክ ብቸኛው የግብጽ አምላክ ሲያደርገው፣ መሐመድ ደግሞ ለዐረቦች ወንድ የነበረውን የጨረቃ አምላክ ብቸኛው የዐረቦች አምላክ አደረገው፡፡ ከሁለቱ የትኛውም ቢሆን የመጽሐፍ ቅዱሱን እግዚአብሔርን በምንም አይመስልም፣ አይገናኝም፤ ሁለቱም ከብዙ አማልክት አምልኮ የተወረሱ ጣዖታት ናቸውና፡፡ ሁለተኛ፣ አኪናቶን አንድ አምላክ አምላኪ ቢመስልም የአምላክነትን ክብር ለራሱ አድርጓል፡፡ መሐመድም ራሱን «አምላክ» ብሎ ባይጠራም በተግባር ግን ብዙ የ«አምላክነት» ክብሮችን ለራሱ ሰጥቷል፡፡ ሦስተኛም፣ አኪናቶን የፀሐይን ቅርፅ በ «ታው» ምልክት ላይ በማድረግ ለአምላኩ ምልክት አደረገ፡፡ መሐመድ ደግሞ የጥንቱን ጣዖታዊ የጨረቃ ምስል ቅርጽ እንዳለ ለ«ብቸኛው አምላክ» ለአላህ ምልክት አደረገላቸው፡፡ ስለዚህ የጣዖታትን ቁጥር መቀነስ ብቻ ወደ እውነተኛው አምላክ አምልኮ አያደርስም፡፡

ከመሐመድ መነሣት በፊት የአላህ ጣዖት መቀመጫ መካ ነበረች፡፡ ስለዚህም ሕዝቡ ሲጸልዩ ፊታቸውን ወደ መካ አዙረው ነበር፡፡ ከእስልምና በፊት ሕዝቡ ፊታቸውን ወደ መካ አዙረው በቀን አምስት ጊዜ ይጸልዩ ነበር፡፡ (The Encyclopedia of Islam p.303)፡፡ ከእስልምና መጀመር በፊት እያንዳንዱ የዐረብ ጎሳ አላህ የየራሱ አማልክት የበላይ እንደሆነ ያስቡ ነበር፡፡ የጨረቃ አምላክ የሆነው የአላህ ምልክት የነበረችው ጨረቃ ነበረች፡፡ ይህም ዛሬም ድረስ ቀጥሏል (ትርጉሙን - ከመካ እስከ ጨረቃ እስልምና ይስፋፋል በሚል ቢቀይሩትም)፡፡ መሐመድ ሌሎቹን ጣዖታት ሲያጠፋ ጥቁሯን ድንጋይ ግን አላጠፋትም፡፡ ስለዚህ ዛሬም ድረስ እስላሞች እርሷን ለመሳም ከየቦታው ይጓዛሉ፡፡ መሐመድ ሌሎችን ጣዖታት ሲያጠፋ ለምን ይህችን ድንጋይ ብቻ አስቀራት?

ለአንድ እስላም፣ በመጽሐፍ ቅዱስ የተገለጸው አንድ የሆነ፣ ነገር ግን በአንድነቱ ውስጥ ልዩ ሦስትነት ያለው እግዚአብሔር ጣዖታዊና ተቀባይነት የሌለው ነው፡፡ ይህም መሐመድ አስቀድሞ ያጠፋቸውን ብዙ አማልክት፣ በተለይም የአላህ ሦስት ልጆች ተብለው ይመለኩ የነበሩትን ስለሚያስታውሳቸው ነው፡፡ የጥንቱ የብዙ አማልክት አምልኮ የፈጠረባቸው ጭፍን ጥላቻ ነው፡፡ አንድ አምላክ የሆነው እግዚአብሔር በአንድነቱ ውስጥ ልዩ የሆነ ሦስትነት አለው የሚለውን የሥላሴ ሀልውና የአንድ አምላክ ሀልውና መሆኑን ባለመረዳት ልክ ሦስት የተለያዩ አማልክት እንደሆኑ አድርገው ነው የሚተረጉሙትና የሚረዱት፡፡ ይህም በቁርአናቸው ተጽፏል፡- «እነዚያ አላህ የሦስት ሦስተኛ ነው ያሉ በእርግጥ ካዱ» ይላል፡፡ ፭፡፸፫፡፡ እኛ እግዚአብሔርን የሦስት ሦስተኛ ነው ብለን ክፍልፋይ አምላክ አናመልክም፡፡ ይህ ደረቅ የስም ማጥፋት ዘመቻ ከመሆን ሌላ ምን ሊሆን ይችላል?

## ፭. «አላህ» የሚለው ስም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ይገኛል?

እስላሞች አላህ የሚለው ስም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ይገኛል ሲሉ ይሰማል፡፡ አላህ በቁርአን አንድ ጊዜም ያህዌ አልተባለም፣ ያህዌም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በጭራሽ አላህ አልተባለም፡፡ ኤሎሂም የሚለው ለያህዌ ተደጋግሞ የተነገረው የዕብራይስጥ ቃልም በቁርአን አንድ ቦታም ላይ አገልግሎት ላይ አልዋለም፣ አልተጠቀሰም፡፡

በመጽሐፍ ቅዱስ ራሱን «ያለና የሚኖር» በማለት የገለጸው አምላክ ራሱን የአብርሃም፣ ይስሐቅና የያዕቆብ አምላክ ነኝ በማለት ገለጸ:: ይህ እግዚአብሔር ኢየሩሳሌምን የዳዊት ከተማ በማለት ይጠራታል:: መሲሑም ከዳዊት ዘር እንደሚወለድ ይናገራል:: እንደተናገረም ተፈጽሟል:: የአላህ ቅዱስ ስፍራ የሚባሉትን፤ መካንም ሆነ መዲናን አንድ ጊዜም አያነሣቸውም:: ኢየሩሳሌምን ግን ስምንት መቶ ጊዜ ያህል ያነሣታል:: ኢየሩሳሌም በቁርአን አልተጠቀሰችም:: ሆኖም እስላሞች የእነርሱ እንደሆነች ይናገራሉ፤ መጽሐፋቸው ግን አንዴም አያነሣትም::

በብሉይ ኪዳን ዘመን እግዚአብሔር የእስራኤላውያን አምላክ ነኝ አለ:: እነርሱም የእርሱ ምርጦች ተባሉ:: እነዚህ እስራኤላውያን የአላህ ምርጦች ግን አልተባሉም::: ይህም በሐዲስ ኪዳን ለክርስቲያኖች ሁሉ ነው:: ታድያ በብሉይ ዘመን አይሁድ፣ በዘመነ ሐዲስ ደግሞ ክርስቲያኖች የእግዚአብሔር ምርጦችና የበኩር ልጆች እንጂ የአላህ አይደሉም:: አላህማ እስላሙን፣ አይሁዳዊንም ሆነ ክርስቲያንን ጓደኛው እንዳያደርግ ይከለክላል:: «እናንተ ያመናችሁ ሆይ፣ ይሁዶችንና ክርስቲያኖችን ረዳቶች አድርጋችሁ አትያዙ» ፭:፶፩::

እስላሞች ከእስልምና ዘመን በፊት አላህ የመጽሐፍ ቅዱሱ ያህዌ (ዘሀሎ ወይሄሉ) - የአባቶች፣ የነቢያትና የሐዋርያት አምላክ እግዚአብሔር ነው ይላሉ:: የእስልምና እምነት ተከራካሪ የሆነው አሕመድ ዲዳት «ሃሌ ሉያ» ("Allelujah") የሚለውን «አላህሉያ» ("Allah-lujah") ወደሚል የግድ በመጠምዘዝ አላህ የመጽሐፍ ቅዱሱ የእግዚአብሔር ስም ነው በማለት ይከራከራል:: (*What is His Name?*, **Durban, SA: IPCI, 1990, p.37**):: «ሃሌ ሉያ» የ ያህዌ Yahweh አጭር መግለጫ - ያህ YAH - ማመስገን (አመስግኑ) በሚለው የዕብራይስጥ ቃል ከመነሻው ሲቀደም የሚገኝ ነው:: በጥሬ ቃሉ ሃሌሉያ ማለት ያህዌን አመስግኑ ማለት ነው:: (alle- ማመስገን - praise, ፣ lu - ለ to, yah - ያህዌ - Yaweh). የቃሉ መጀመሪያ Hallel - ሀለል- ሲሆን ይህም ማመስገን ማለት ነው:: ይህም ከአላህ ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት የለውም:: የመጨረሻው ቃል ያህ - ደግሞ ያለና የሚኖር ሕያው የሆነውን አምላክ የሚያመለክት ነው:: አሕመድ ዲዳት አራማይክንና ዐረብኛን በመደባለቅ ምናልባት ከርሱ ያነሰ ዕውቀት ያለው ሰው ቢያገኝ አለማወቁን ተጠቅሞ ለማምታታት ነው:: ከሌላ ቋንቋ የተገኘ ቃል አነባበቡ ከአንድ ሌላ ቋንቋ ቃል ጋር ቢመሳሰል እንኳ አጋጣሚ ሊሆን ይችላል እንጂ የንባብ መመሳሰል የትርጉም ወይም የአሳብ መመሳሰልን አያመለክትም:: እንደ ዲዳት ያሉ እስላሞች ግን የሌላን ቋንቋና ባህል፣ ቃላትና ትርጉሞች የሚመሳሰሉ መስለው ከታዩዋቸው፤ የራሳቸውን መጽሐፍም ሆነ እምነት አስረጂዎች ለማስመሰል ይሞክራሉ:: ይህ የሚያሳየው ዲዳት ዕብራይስጥና አራማይክ የማያውቅ ብቻ ሳይሆን ደፋር አላዋቂ መሆኑንም ነው::

እንዲሁም ይኸው ሰው አላህ የሚለው ቃል ከጣዖት አምልኮ ባህልና ታሪክ ፈጽሞ የጸዳና የጠራ እንደሆነ ይገልጻል:: «አላህ የብቸኛው አምላክ ልዩና ብቸኛ ስም ነው:: ... ማንም ለአላህ አነስታይ ፆታ ሊናገርለት አይችልም» ይላል ዲዳት:: ከአላህ ልጆች አንዲቷ የአላህ አነስታይ ፆታ መግለጫ በሆነ ስያሜ አል-ላት ትባል የነበረ መሆኑን ግን ለአንባቢዎቹ አይነግራቸውም::

ለስም አጠራሩ ክብርና ምስጋና ይግባውና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የእነርሱን አምላክ ስም እንደጠራ ለማድረግ ሲሞክሩ የቃላት ጨዋታው የበለጠ አስቂኝ ይሆናል:: ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ሳለ «ኤሎሄ ኤሎሄ ላማ ሰበቅታኒ» በማለት የጠራው የእነርሱን አምላክ እንደሆነ ያወራሉ:: ሐዲስ ኪዳን የተጻፈው በግሪክ ቋንቋ ሲሆን ጌታችን በአራማይክ ቋንቋ የተናገረውን ነው የሚያሳየን:: ጌታችን በመዝሙር ፳፩÷፩ ላይ የተነገረውን የሰውን ልጆች ጩኸት በሙሉ ነው እኛን ወክሎ የጮኸው:: ይህም ከአራማይክ ቋንቋ በድምፀ ንባብ ማጠጋጋት ዐረብኛ ቃል ለማግኘት የሚደረግ አስቂኝ ሙከራ ነው:: ይህን መላ ምታቸውን የበለጠ ትርጉም የለሽ የሚያደርገው ደግሞ በመስቀል ላይ የተሰቀለው ኢየሱስ መሆኑን የማያምኑ መሆናቸው ነው:: መጽሐፋቸው የተሰቀለው ኢየሱስ ሳይሆን በእርሱ ቦታ ሌላ ሰው ተተክቶ ነው ይላልና:- «እኛ የአላህን መልክተኛ የመርየምን ልጅ አልመሲሕ ዒሳን ገደልን በማለታቸውም (ረገምናቸው)፣

አልገደሉትም፤ አልቀሉትም፤ ግን ለነሱ የተገደለው ሰው በዒሳ ተመሰለ ... በእርግጥም አልገደሉትም) ፬:፻፶፯:: ታዲያ የእነርሱ «ዒሳ» በመስቀል ላይ ካልተሰቀለና ካልሞተ ኤሎሄ የሚለው የአራማይክ ቃል፤ አላህ ከሚለው የዕረብኛ ቃል ጋር በድምፀ ንባቡ ትንሽ ስለተ ቀራረበ ብቻ አሁን ለዚህ ሲሉ ሊሰቅሉት ይገባል?

## ቁርዓን ከሰማይ የወረደ ነውን?

የቁርዓን እያንዳንዱ ክፍል «አያ» ይባላል:: ይህም በዐረብኛ ተአምር ማለት ነው:: መሐመድ ቁርአን የእሱ ብቸኛ ተአምር መሆኑን ይናገራል:: ሆኖም ቁርአን በእርሱ የሕይወት ዘመን በመጽሐፍ መልክ አልነበረም:: በቁርአን የይዘት ቅደም ተከተል ላይ ያለው ልዩነት ዋናው ምክንያት የመጨረሻውን የቁርአን ስብስብ ይዘትና ቅደም ተከተል ለማጽደቅ ወይም ይሁንታ ለመስጠት መሐመድ በሕይወት ያልነበረ መሆኑ ነው::

እንደ እስልምና እምነት ቁርአን በሰማይ ባለ ጽላት ላይ ተቀርፆና ለዘላለም ተጠብቆ የሚኖረው የአላህ የመጨረሻ መገለጥ መጽሐፍ የቃል በቃል ቅጂ ነው:: ፹፭:፳፩-፳፪:: ቁርአን የዘላለማዊ ሰማያዊ መጽሐፍ፣ ሥርዓተ ነጥብ፣ ምዕራፍ፣ አከፋፈልና ርእስ ሳይቀር የዛ አንድ ዓይነት ግልባጭ ነው ብለው ያምናሉ:: እንደ እስልምና ትውፊት እነዚህ «መገለጦች» ከሰባቱ ሰማያት ውስጥ የታችኛው ወደሆነው የተላኩት (የወረዱት) በረመዳን ወር ሌሊት ነው:: ፲፯:፹፭:: (Pfander, C. G., The Mizanu'l Haqq, (Balance of Truth), London, The Religious Tract Soc., 1910 ከዚያም ለመሐመድ በሂደት እንዳስፈላጊነቱ በመልአኩ በጂብሪል አማካይነት ተገለጠለት:: ስለዚህ በቁርአን ላይ ያለው እያንዳንዱ ቃልም ሆነ ሆሄ ከሰው ተጽእኖ ነጻ ነው ይላሉ::

ሆኖም ይህ የቁርአን መገለጥ ሂደት ምንጩና ማስረጃው ተገለጠለት የተባለው ራሱ መሐመድ ብቻ ነው:: ከራሱ ሌላ ይህንን የሚያስረዳ ተገለጠለት ከተባለው ጊዜ በፊትም ሆነ ተገለጠለት በተባለው ጊዜ ምንም ዓይነት ተአምራትም ሆነ ትንቢት ወይም ሌላ ማስረጃ የለም:: በመጽሐፍ ቅዱስ ለእግዚአብሔር መገለጥ እንደምናገኘው ብዙ ዓይነት ማስረጃ (ታሪክ፣ ከዚያ በፊት ከተደረጉ የእግዚአብሔር መገለጦች ጋር የሚስማማና የማይቃረን መሆን፣ ከእግዚአብሔር የተላከ መሆኑን ለማሳየት የሚፈጸሙ ተአምራት፣ በየዘመኑ የተፈጸሙና ዛሬም ወደፊትም እየተፈጸሙ ያሉና የሚፈጸሙ ትንቢቶች፣ ወዘተ) በቁርአን ጨርሶ አይገኙም:: በመሐመድ ነቢይነትና በቁርአን እነዚህ ማስረጃዎች ስለሌሉ ለክርስቲያኖች በሰው ተጽእኖ ሥር የወደቀና ሰብአዊ የሆነው መጽሐፍ፣ መጽሐፍ ቅዱስ ሳይሆን ቁርአን ነው::

ታዲያ በቁርአን ያሉትን ብዙ ችግሮች ምን እናድርጋቸው? ምንስ እንበላቸው? እንዲህ እንደሚባልለት ከሰማይ የወረደና ፍጹም መጽሐፍ ከሆነ ከሰዎች የሚነሣበትን ትችት ሊያልፍና ከስሕተት ነጻ ሊሆን ይገባዋል:: በውስጡ ያሉ ብዙ ልዩነቶችን፣ የእርስ በርስ ግጭቶችንና ስሕተቶችን እንዴት እናድርጋቸው?

### የቁርአን ልዩ ጠባይአት (ቁርአንን ልዩና ሰማያዊ ያደርጉታል) የሚባሉት ነገሮች

ሀ. ቅድስናው: - እስላሞች ብሉይ ኪዳንንና ሐዲስ ኪዳንን እናከብራለን የሚሉ ቢሆንም፣ ለቁርአን ግን ልዩና ከሁሉም ነገር በላይ የሆነ ቦታ ይሰጣሉ:: የመጻሕፍት ሁሉ እናት ይሉታል:: ፵፫:፫:: ይዘቱን መመርመር ድፍረትና ኃጢአት ነው:: በጥንቃቄና በንጽሕና እንጂ እንዲሁ እንደተገኘም አይነካም::

ለ. ልዩ የሆነ የሥነጽሑፍ ዘይቤው: - ለብዙ እስላሞች ቁርአን ከሌሎች መገለጦች የሚበልጠው በመጠቀ የሥነ ጽሑፍ ዘይቤው ነው:: ቁርአንን የሚስተካከል ሥነጽሑፍ ስለሌለ፣ ቁርአን ከአላህ የወረደ ተአምር ነው ይላሉ:: ሆኖም በቁርአን የተገለጹት ብዙ ታሪኮችና አንቀጾች አንዳንዴ ቃል በቃል፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ አሳብ በአሳብ ከተለያዩ የሁለተኛው መቶ ዓመት የአይሁድና የዞራስትሪያን አዋልድ ድርሳናት የተቀዱ ሆነው እናገ ኛቸዋለን:: እንዲሁም ቁርአን በአንድ ሰው - በመሐመድ - የተጻፈ ሳይሆን ከእርሱ ሞት በኋላ ባሉት ፲፬ እስከ ፳ ዓመታት ውስጥ በተለያዩ ሰዎች የተሰበሰበው ቁርአን በአንድ

ሰው የተጻፈ ተአምር ሲባል ይችላል ወይ? ብለን እንድንጠይቅ ያደርገናል። ቁርአን በመሐመድ ጊዜ እንኳ በአንድ መጽሐፍነት ተዘጋጅቶ በጥራዝ መልክ አልነበረም። አንድ መጽሐፍ ሆኖ ቀኖናዊ የተደረገው ወደ ስምንተኛውና ዘጠነኛው መቶ ዓመት ላይ ነው።

እንደሚባለው የሥነጽሑፍ ዘይቤው የመጠቀ ነው የሚለውን አባባል እንዳለ ብንቀበለው እንኳ (ለነገሩ ይህም አይደለም፣ ምክንያቱም ብዙ የሰዋሰው ግድፈቶች አሉበት፣ የድግግሞሹ ነገር የአንባቢን ትዕግስት ይፈታተናል፣ ታሪካዊም ይሁን አመክንዮታዊ ቅደም ተከተል የለውም ወዘተ) ጥሩ ሥነጽሑፍ መሆን የመለኮታዊ (አምላካዊ) መገለጥ ነው ለመባል በቂ ማስረጃ ነው ወይ? በየቋንቋውና በየባህሉ ታላላቅ ሥነጽሑፎች አሉ። ለምሳሌም በሕንድ - ሪግ ቬዳ (፩ሺሕ-፲፭፻ ቅ.ል.ክ.)፣ በግሪክ -የሆሜር ኦዴሴይና ኢሊያድ፣ የሀሙራቢ ኮድ፣ የጊልጋሜሽ ኤፒክ እና የሙት መጽሐፍ የተባለው ከግብፅ - እነዚህ ሁሉ በሥነ ጽሑፍ ዘይቤአቸው የሚደነቁ ሲሆኑ ሁሉም በዘመን ቁርአንን ይቀድሙታል። ከቅርብ ዘመን ሥራዎችም እንደ የሼክስፒር ሥራዎች ያሉ የሥነ ጽሑፋቸው ዘይቤ ታላቅ ነው የሚባሉ አሉ። ሆኖም ከእነዚህ አንዱንም መለኮታዊ ናቸው ያለ ማንም የለም።

ሐ. ቋንቋው ዐረብኛ መሆኑ፡ - ዐረብኛ የአላህ ቋንቋ መሆኑን እስላሞች ያምናሉ። ስለዚህም በዐረብኛ የሆነው ቁርአን ትክክለኛ የአላህ መጽሐፍ ነው። ግን በቁርአን ውስጥ ምንም ዓይነት ከዐረብኛ ውጭ የሆነ ቃል የለም? አለ እንጂ። ለምሳሌም፣ ፈርዖን (የግብጽ ቃል - ንጉሥ ወይም ገዢ ማለት ነው) ሰማንያ አራት ጊዜ ተደጋግሞ ይገኛል። አዳምና ኤደን የአካዲያን ቃላት ሲሆኑ ፳፬ ጊዜ ይገኛሉ። ኤደን በዐረብኛ ጃና - ማለት የተክል ቦታ ነበር መሆን የነበረበት። አብርሃም ከአሶራውያን ቋንቋ የመጣ ቃል ነው። ትክክለኛው የአረ ብኛ ቃል አቡ ራሂም ነበር። የፋርሳዊያን ቃላት ደግሞ ሃሩትና ማሩት፣ ሲራት፣ ጂን የሚሉት ይገኛሉ። ከሱርስት ደግሞ ታቦት፣ ዘካት፣ ማልኩት የሚሉት ቃላት ተወስደው በቁርአን ውስጥ ይገኛሉ። ከዕብራይስጥ ተውራት፣ ሳኪናህ፣ ሀበር፣ ሌሎችም ቃላት ይገኛሉ። ከግሪክ ኢንጂል (ወንጌል ማለት ነው) ኢብሊስ ደግሞ ከግሪኩ ዲያብሎስ የተወረሰ ነው። ከግእዝ ደግሞ መልአክ (፪:፴፫) ተወስዶአል።

## የቁርአን መጽሐፍ ጥራዝ አሰባሰብ ታሪካዊ ሂደት

እንደ እስልምና ትውፊት የሱራዎቹን (መጻሕፍቱን) መገለጥ መሐመድ የተቀበለው በጂብሪል መልአክ በሦስት ጊዜያት ውስጥ ነው። የመጀመሪያው የመካ ጊዜ ሲባል ከ፮፻፲፩-፮፻፲፭ ድረስ ያለው ነው። በዚህ ጊዜ ያሉት ሱራዎች በቁርአን ያሉት ብዙዎቹ ማስጠንቀቂያዎችና አላህን በተመለከተ ድምድሜያቸውን አመላካች በሆኑ ገሬ ገለጻዎች ያሉበት ነው። ሁለተኛው ጊዜ ደግሞ ሁለተኛው የመካ ጊዜ ተብሎ የሚታወቅ ሲሆን (፮፻፲፭-፮፻፳፪) ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ምንጮችን የሚመስሉ ዶግማ ነክ ጉዳዮች ያሉበት ነው። እስልምና ብቻውን ትክክለኛ ሃይማኖት ነኝ ማለት የጀመረው በዚህ ጊዜ ነው። ሦስተኛው ገዚ የመዲና ጊዜ የሚባለው ሲሆን፤ (፮፻፳፫-፮፻፴፪) መዲናን ያማከለና እስከ መሐመድ ሞት ያለው ጊዜ ነው።

### ፩. የአሰባሰቡ ዘዴ ወይም አካሄድ

መሐመድ በርግጥ «አምላካዊ መገለጥ» ወይም «ራእይ» የተቀበለ ስለመሆኑ ብዙ አከራካሪ ነገሮች ያሉ ቢሆንም፤ ዛሬ ያለው ቁርአን እርሱ ተቀብሎታል የሚባለውን ነገር ሁሉ እና ያንን ብቻ ይዟል ወይ? ስለሚለው ጉዳይ ደግሞ የበለጠ ጥርጣሬና ጥያቄ አለ። እንደ የእስልምና ትውፊት መሐመድ ሞቱን አስቀድሞ ስላላወቀ ራእዮቹን በአንድ መጽሐፍ (ጥራዝ) ለማድረግ አልተዘጋጀም ነበር። ስለዚህ የተባለውን ነገር የመጻፉና የማሰባሰቡ ነገር የመሐመድ ተከታዮች ሓላፊነት ነበር። ከዘጠኝ እስከ አሥረኛው መቶ ዓመት የነበረውና ከእስልምና ትውፊቶች ታሪክ አሰባሳቢዎች ታዋቂና ተአማኒነት የነበረው አል ቡካሪ የተባለው እስላም ምሁር፤ መሐመድ ራእይ ወይም ተመስጦ ድንገት ሲመጣበትና ራሱን ወዳለማወቅ ደረጃ ሲደርስ የተገለጠለት ነገር በጊዜው በተገኘ በማንኛውም ነገር ላይ

ይጻፍ ነበር:: የሞቱ እንስሳት እግርና ጭን፣ የዛፎች ቅጠል፣ ብራና፣ ቆዳና ድንጋይ ሳይ ቀር ለመጻፊያ ይጠቀሙ ነበር:: የሚጻፍበት ምንም ነገር ባልነበረ ጊዜ ደግሞ በተቻለ መጠን እንዳለ ለመሸምደድ ይሞክሩ ነበር:: ዋና ዋናዎቹ ደቀ መዛሙርቱም አብዱላህ ኢብን ማሱድ፣ አቡ ሙሳ፣ ኡባይ ኢብን ካአብ ሲሆኑ ሁሉም የመሐመድ የቅርብ ሰዎች ነበሩ::

እንደ ሳሂሪ ቡካሪ፣ መሐመድ ከሞተበት ጊዜ ጀምሮ ባሉት ዓመታት በቃላቸው አጥ ንተው የነበሩት ብዙዎቹ የቅርብ ሰዎቹ በያማማ ጦርነት ላይ በሞቱ ጊዜ ብዙ የቁርአን አንቀጾች ላይገኙ ጨርሰው ጠፍተዋል:: ይህ ድርጊት ከቁርአን ቅጽበታዊ መገለጥ መፈ ጸም ጋር ተደምሮ የመገለጡ መካከለኛ ወይም ነቢይ ከነበረው ከመሐመድ መሞት ጋር ሲጨመር የመሐመድ የቅርብ ሰው የነበረውንና ሀዝራት የሚባለውን ያሉት መገለጦች እንዲሰበስቡ በጊዜው የነበረውን ካሊፍ አቡበከርን እንዲጠይቅ አስገደደው:: መጀመሪያ ላይ ካሊፍ አቡበከር መሐመድ ራሱ ያላደረገውን ነገር ለማድረግ ፈቃደኛ ባለመሆን ይህንን ጥያቄ ለመቀበል ፈቃደኛ አልነበረም:: ኋላ ግን ቁርአንን በቃላቸው ያጠኑት ብዙ ዎቹ በያማማ ጦርነት ሲሞቱ በተፈጠረው ችግር ምክንያት አሳቡን ለወጠ:: የመሐመድ ጸሐፊ የነበረው ዛይድ ኢብን ጣቢት የመሐመድን አባባሎች መገለጦች እንዲያሰባስብና በአንድ ጥራዝ (መጽሐፍ) መልክ እንዲያስቀምጥ በአቡበከር ታዘዘ::

## ፪. የዛይድ ስበስብ

የዛይድ መልስ፣ እንደ ቡካሪ አገላለጽ ደስ የሚል ነው:: የቁርአንን ሱራዎች ከመ ሰብሰብ ይልቅ ተራራ እንዲያንቀሳቅስ ቢታዘዝ ኖሮ ይሻለው እንደነበር መግለጹ ይነገ ራል:: የቁርአንን አንቀጾች ሲፈልግ የሞቱ እንስሳትን ስኮናና ጭን፣ ቅጠሎችንና ብራና ዎችን፣ ቆዳዎችን፣ ድንጋዮችን፣ ወዘተ እና የነቢዩ የቅርብ ሰዎች በቃል ያጠኗቸውን ሽምደዳዎች እንደ ምንጭ ለመጠቀም መገደዱን ስናይ የዚህ አባባሉ ምክንያት ግልጽ ይሆ ንልናል:: (Bukhari, Vol. 6, p. 477)

ይህ የሚያሳየው በዚያን ጊዜ ቁርአንን በሙሉ በቃላቸው የያዙ እስላሞች ያልነበሩ መሆኑን ነው:: እንዲያ ባይሆን ኖሮ የማሰባሰቡ ሥራ ቀላል ይሆን ነበር:: ቁርአንን ሙሉ በሙሉ በቃላቸው የያዙት ሰዎች ቢኖሩ ኖሮ ከእነዚህ ወደ አንዳቸው ሄዶ የሚነ ግሩትን በጻፈ ነበር:: ነገር ግን ይህ ባለመሆኑ ወደ ስኮናዎችና ቆዳዎች እንዲሁም የተ ወሰኑ ክፍሎችን ወደያዙ ግለሰቦች በመሄድ መፈለግ ግድ ሆነበት:: ምንጭ ሊሆን ከሚ ችለው ነገር ሁሉ መፈለግ ነበረበት:: እነዚህ ምንጮች በምንም ሚዛን ቢሆን በሰማይ ለሚኖረው መጽሐፍ «ፍጹም» ቅጂ ናቸው ለሚባሉት መጻሕፍት አስተማማኝና ጥር ጣሬ የማያሳድሩ ምንጮች መሆናቸው አስቸጋሪ ብቻ ሳይሆን ለወግ እንኳ የማይመች ነው::

የዚያድ የመጨረሻ ስብስብ ሙሉስ ለመሆኑ፣ እንዲሁም ትክክለኛ ስለመሆኑ ማስተ ማመኛው ምንድነው? ዚያድ የመሐመድን አባባሎችና ራእዮች ሁሉንም ለማግኘቱ ምንም አሳማኝ ነገር የለም:: የመሐመድ «መገለጦች» ከተጻፈባቸው አንዳንዶቹ አልጠፉ ወይስ አልተበላሹ ይሆን? ከአንቀጾቹስ በያማማ ጦርነት ከተገደሉት ጋር አብረው የሞቱ (የጠፉ) ላለመኖራቸው ምን ዋስትና አለ? ከመልስ ይልቅ በብዙ ጥያቄዎች እንከበባለን:: በሳሂሪ ቡካሪ፣ ዛይድ የሱራ ዘጠኝ የመጨረሻ አንቀጾች (አንቀጽ ፻፳፰ እና ፻፳፱) ከአንድ ግለሰብ ያገኛቸው መሆኑን እንደተናገረ ይገልፃል:: (Bukhari, Vol. 6, p. 478) ከዚያም ይህን አን ቀጽ ከሌላ ከማንም ያላገኘው መሆኑን ይናገራል:: ማለትም ይህን ቃል የሚያውቀው ሌላ ማንም አልነበረም:: ስለሆነም ከዚያ ግለሰብ ባያገኘው ኖሮ እነዚህ አንቀጾች ጠፍተው ይቀሩ ነበር ማለት ነው:: ቁርአን ከሰማይ የወረደ ነው መባሉ ቀርቶ በሰዎች የተጻፈና የተ ሰባሰበ መሆኑን ቢናገሩ በርግጥ እነዚህ ችግሮች በጣም ከባድ ላይሆኑ ይችሉ ይሆናል:: ነገር ግን በአሳህ ዘንድ ያለው የሰማያዊው መጽሐፍ ብቸኛና ትክክለኛ ቅጂ ነው ለሚባል መጽሐፍ ግን፣ ይህ ሁሉ ቀርቶ አንዱም ቢሆን ለመቀበል የሚከብድ ነገር ነው::

ይህ የሚመራን ወደ አንድ መደምደሚያ ብቻ ነው:- ይህን በመጨረሻ የተሰባሰበው ቁርአን ሙሉ ስለመሆኑ መቼም ቢሆን እርግጠኛ መሆን የማይቻል መሆኑን ነው:: ዛይድ ያን አንቀጽ ከአንድ ሰው አገኘ:: ይህም የሚያስረዳው ቁርአንን ሙሉ በሙሉ በቃሉ ያጠናውና የሚያውቀው ሰው ያልነበረ መሆኑንና የዛይድም ስብስብ ሙሉ ይሁን ወይም

አይሁድን መመስከርና መናገር የሚችል ሰው ያልነበረ መሆኑን ነው:: ስለሆነም የቁርአን የመጨረሻ ስብስብ በእግዚአብሔር መገለጥ ላይ ሳይሆን፤ በአንድ ሰው (በዛይድ) አስተ ሳሰብና ጥረት ላይ የተመሠረተ ነው:: ከተለያዩ ቁሳቁሶችና ግለሰቦች ያገኘውንና ሊደርስ በት የቻለውን ያህል አሰባስቦ ሙሉ ቁርአን ነው ያለውን አስቀመጠ:: ይህ መጽሐፉ (ቁርአን) ያን ጊዜም፣ ዛሬም ሁል ጊዜም ሙሉ ነበር ብለው በድፍረት በሚናገሩ እስላ ሞች ፊት ያለ እውነታ ነው:: የዛይድ ስብስብ ከመሐመድ ሚስቶች አንዷ ለነበረችውና የሁለተኛው ከሊፋ የኡመር ልጅ ለነበረችው ለሀፍዛ ተሰጠ::

## ፫. ተፎካካሪ ስብስቦች

በዛን ዘመን የእስልምና እምነት ተከታዮች በነበሩባቸው የተለያዩ ቦታዎች ዘንድ የተ ለያዩ የቁርአን ምንባባት ነበሩ:: የተለያዩ የመሐመድ የቅርብ ሰዎች እያንዳንዳቸው የየራ ሳቸውን ስብስብ አዛጋጅተው ነበር:: ዚያድ በአቡበከር ትእዛዝ ኦፊሴላዊ የሆነ ስብስብ ቢያዘጋጅም እንደርሱ ያሉ ሌሎች ስብስቦች (ቁርአኖች) ነበሩ:: ከእነዚህም በጣም ታዋቂ የነበሩት ሁለቱ ስብስቦች አንዱ በኢራቅ አካባቢ ከፍተኛ ተቀባይነት የነበረው የአብዱላህ ኢብን ማስ‌ድ ስብስብ ሲሆን ሌላው ደግሞ የሶርያ ዋና ቁርአን የሆነው የኡባይ ኢብን ካአብ ነበር::

## ፬. የመጻሕፍቱ (ስብሰቦቹ) አንድ ወጥ መደረግ (The Standardization of One Text)

በሦስተኛው ከሊፋ በኡትማን ዘመን ቁርአንን አንድ ወጥ ለማድረግና በእስልምናው ዓለም አንድ ዓይነት መጽሐፍ ብቻ እንዲኖር ለማድረግ ቁርጠኛ ሥራ ተሠራ:: ከሀፍዛ የተገኘው የዛይድ ስብስብ በካሊፋ ኡትማን ለዚህ ጉዳይ ተመረጠ:: ሆኖም ማሱድ ሰባ ሱራዎችን በቃሉ አጥንቶ በነበረበት ጊዜ እንኳ ዛይድ ገና ያልተወለደና ከማሱድም ሆነ ከካአብ አንፃር በዕድሜው ልጅ ስለነበር፤ የእርሱ ስብስብ መመረጡ ማሱድንና ካአብን አስቆጥቷቸዋል:: በቃል ታሪክ መሠረት የዛይድ ስብስብ በኡትማን የተመረጠው የተ ጠቀመው ቋንቋ በመካ የተለመደውና የዐረብኛ መስፈሪያ ተደርጎ የተወሰደው የቋሪሽ ዘዬ በመሆኑ ነበር:: እንደ ሌሎቹ እንደ ሁለቱ ሁሉ ይህም በመሐመድ ትክክለኛ ነው ተብሎ ያልተመረጠ ወይም ያልተመሰከረለት ሲሆን፤ በኡትማን ትእዛዝ የዛይድ ስብስብ (መጽ ሐፍ) ተመረጠ:: በቀጣይም የዛይድ መጽሐፍ ቅጂዎች በእያንዳንዱ የእስላም ግዛት ተ ሰራጨ፣ የእነ ማሱድና የእነ ከአብን ጨምሮ ሌሎች ቁርአን ነን የሚሉ መጻሕፍት ግን እየተፈለጉ ተቃጠሉ:: የሌሎች ስብስቦች መቃጠል የቁርአንን መጽሐፍ ወጥ ለማድረግ የተወሰደ እርምጃ ነው:: ዛሬ ያለው አንድ ወጥ ቁርአን ብቻ ሊሆን ቢችልም ይህ ግን ከመጀመሪያው ጋር አንድ ለመሆኑ ምንም ማስረጃና ማመሳከሪያ የለም:: ትክክለኛው ለመሆኑ ምን ማስረጃ አለ? ልናመሳክርበት የምንችል ሌላ ዓይነት የጥንት ቅጂ ስለሌለ (በኡትማን ስለጠፉ) ማወቅ አንችልም::

## ፭. የጠፉ አንቀጾች

የጠፉ አንቀፆች ጉዳይም ወደ ሌላ አስቸጋሪ ፈተና ይወስደናል:: ዛይድ ኢብን ጣቢት በሰ በሰበውና ባዘጋጀው ስብስብ ውስጥ፤ የመሐመድን ራእዮች በሙሉ ያካተታቸው ስለመ ሆኑ እንዴት እርግጠኛ መሆን እንችላለን? እውነታው መሆን አንችልም» ነው:: ስለሆነም ይህንን እንዲነግረን በእስልምና ትውፊት ላይ መመሥረት ግድ ይሆንብናል:: ሆኖም የእስልምና ትውፊት ራሱ ዛይድ በራሱ ስብስብ ላይ ጥርጣሬ እንደነበረው ይነግረናል::

*ሱራ ፴፫:፳፫::*

እንደ ሳሂህ ቡካሪ፣ የዛይድ መጽሐፍ ተቀድቶ ወደ ሰባቱም የተለያዩ ከተሞች የተላከ ቢሆንም፤ ዛይድ መሐመድ ያለው ቃል ከእርሱ መጽሐፍ ውስጥ ያልተጨመረ መሆኑን በድንገት አስታወሰ:: ያልተጨመረው አንቀጽ የሱራ ፴፫ ቁጥር ፳፫ አንቀጽ ነው:: ከዚ ያም ይህን ቃል ከኢብን አል አስናሪ እስኪያገኘው ድረስ ጠብቆ ፈለገው ይላል:: የቁርአን ብቸኛና ትክክለኛ ቅጂ ተብለው ከተሰራጩ በኋላ እንኳ ዛይድ የተረሳ ቃል ከአንድ ሰው ያገኘ መሆኑን እናያለን:: ይህም በስብስቡ ሂደት ከአንድ ሰው ብቻ እንደተገኘው ቃል

ዓይነት ነው። ስለዚህ የተሳኩት ሰባቱ ቅጂዎች ሙሉና ፍጹም አልነበሩም ማለት ነው። የበለጠ የሚያሳስበው ደግሞ የቁርአን ስብስብ የተመሠረተው በአንድ ሰው የመሰብሰብና የማስታወስ ችሎታ የመሆኑ ጉዳይ ነው። ቁርአንን በሙሉ በቃሉ የያዘ ሰው ያልነበረ የመሆኑ ነገር ግልፅ ነው። ሌሎች የተረሱ ወይም የተዘለሉ አንቀፆች ላለመኖራቸው ምን ማረጋገጫ አለ? የዚህን ጥያቄ መልስ ከሌላ የእስልምና ትውፊት፣ ከሳሂ ሙስሊም ማግኘት ይቻላል።

## ስለ ውግረት የተነገሩ አንቀጾች

ሳሂ ሙስሊም እንደሚለው ከዚያድ መጽሐፍ ውስጥ ሳይካተቱ የቀሩ አንቀጾች ነበሩ። ከእነዚህም አንዱ ስለ ውግረት የተነገረው አንቀጽ ነው። ብዙዎቹ ትውፊቶች ስለዚህ ስለ ተዘለለው አንቀጽ ይናገራሉ። እንደ ኢብን ኢሳቅ አገላለጽ እንዲህ እናነባለን፡-

«አላህ መሐመድን ላከው፣ ለእርሱም መጻሕፍትን አወረደለት። ካወረደለት ውስጥ አንዱ ክፍል ስለ ውግረት የሚናገረው ክፍል ነበር። ኡማር እንዲህ ይላል፡- «ተምረነዋል፣ እናነበዋለን፣ ልብ ብለንም እንገነዘበዋለን። ነቢዩ (መሐመድ) ወግሯል፣ እኛም እርሱን ተከትለን ወግረናል። ነገር ግን በሚመጣው ዘመን ሰዎች በአላህ መጽሐፍ ውስጥ ውግረትን በተመለከተ ምንም ነገር አላገኘንም በማለት አላህ የሰጠውን ትእዛዝ ችላ እንዳይሉና እንዳይሳሳቱ እሰጋለሁ። በአላህ መጽሐፍ የተገለጸው ውግረት በሚያመነዝሩ ባለ ትዳሮች ላይ የታዘዘ ቅጣት ነው።»

ስለዚህ እንደ ኡማር ገለጻ የውግረት አንቀጽ የመጀመሪያው ቁርአን ላይ የነበረ ሲሆን አሁን ካለው ቁርአን ግን የለም። በብዙዎቹ የቃል ታሪኮች አመንዝረዋል የተባሉ ብዙ ሴቶችና ወንዶች በመሐመድና በተከታዮቹ የተወገሩ ስለመሆናቸው ይነገራል። ሆኖም ዛሬ ግን በቁርአን፣ ሱራ ፳፬፡፪ ላይ የዝሙት ቅጣት አንድ መቶ ግርፋት (ጅራፍ) መሆኑን እናነባለን። ኡመር ዝሙት ውግረት የሚገባው ታላቅ ኃጢአት ነው ይላል። ሆኖም ይህ አንቀጽ ከዛሬው ቁርአን የለም። ጉዳዩንም ያነሣው ለዚህ ነው። አሁን ያለው ቁርአን በመሐመድ ለተከታዮቹ የተላለፈው ስለመሆኑ እስላሞች ራሳቸውን ሊጠይቁ ይገባቸዋል። እንዲህ ባሉ ማስረጃዎች ፊት ዛሬ ያለው ቁርአን የበለጠ ጥያቄ ምልክት ውስጥ ይገባል። ታዲያ ይህ ሁሉ ነገር «ከሰማይ ለወረደ» መጽሐፍ ይስማማል?

ይህም ብቻ አይደለም። የኡቱማን ቁርአን ከእርሱ ሞት በኋላም የከሊፋዎችን የአንድ ወጥ መጽሐፍ መስፈሪያ ለማሟላት ሲከለስና ሲስተካከል ነበር። አል ሀጂጂ የተባለው የኩፋ ገዢ አሥራ አንድ የተለያዩ ማስተካከያዎችንና እርማቶችን አድርጓል። ሆኖም እነዚህ እርማቶችና ማስተካከያዎች በኋላ ወደ ሰባት ተቀንሰዋል። ሌሎቹ ጥንታውያን ስብስቦች ኖረው ቢሆን ኖሮ የትኛው ከጥንቱ ጋር እንደሚቀራረብ ማመሳከር ይቻል ነበር። ነገር ግን የመጨረሻው መጽሐፍ የተወሰደበት የአፍዛ ቅጂ እንኳ በኋላ ሚርቫን በተባለው የመዲና ገዢ እንዲጠፋ ተደርጓል። ግን ለምን?

እነዚህ ድርጊቶች በተለያዩት ቅጂዎች መካከል ቅራኔና ልዩነት የነበረ መሆኑንና ሌሎቹን አጥፍቶ አንዱን ብቻ መምረጥ የግድ አስፈላጊ ነው ብለው ስላመኑ እንደሆነ አያሳይምን? ሌሎቹ ለምን ተቃጠሉ? በተጨማሪም መሐመድ በሌለበት ሁኔታ (ከሞተ በኋላ) ኡትማን እንዴት አድርጎ አንዱን ከሌላው መለየትና መምረጥ ቻለ? ስለዚህ በመጽሐፍ ቅዱስ ማድረግ እንደሚቻለው ዓይነት የዛሬውን ቁርአን ተአማኒ ለማድረግ ልናመሳክርበት የምንችለው ሌላ ጥንታዊ ጽሑፍ የለም።

ብዙ ቅጂዎች ባሉ ቁጥር የጥንታዊነቱ እርግጠኛነት የበለጠ አስተማማኝ ይሆናል። ቁርአን አንድ ብቻ (የዛይድ ቅጂ) ነው ያለው። አዲስ ኪዳን ደግሞ ወደ ሃያ አራት ሺሕ የሚደርሱ ጥንታውያን የሆኑ የተለያዩ ቅጂዎች ይገኛሉ። የመጽሐፍ ቅዱስና የቁርአን በዚህ ረገድ እንኳ ያለው ልዩነቱ ይህን ያህል ነው። ዛሬ በእስላሙ ዓለም የሚነበበውና ጥቅም ላይ የሚውለው ቁርአን በኡትማን የተመረጠውና በኋላም በአል ሃጂጂ የተስተካከለው የዚያድ ቁርአን ነው። ስለሆነም አሁን ያለው አንድ ወጥ መጽሐፍ በመለኮታዊ ዐዋጅ ወይንም በመሐመድ ውሳኔ ሳይሆን በሰዎች በተደረጉ የማሰባሰብ፣ የማስወጣትና የማስገባት ሂደታዊ ማስተካከያዎችና ውሳኔዎች የተጠናቀረ ነው።

# የቁርአን ምንጮች

የስብስቡን ሂደት ስናይ የተረሱና የተዘለሉ ነገሮች የነበሩ መሆናቸውንና ስብስቡም በአንድ ጊዜ በተአምራት ያለቀ ባለመሆኑ ብዙው ይዘቱ ቀስ በቀስ ወደ ኋላ ላይ የተጨመረ ነው ብለን እንድንደመድም የሚያስገድደን ሁኔታ የሚፈጥር መሆኑን አይተናል:: በቁርአን የምናገኛቸው ታሪኮችና አሳቦች ከየት ተገኙ? ምንጫቸውስ ምንድነው? ከዚህ ዓለም የሌሉ ሰማያውያን ናቸው? ወይስ ከተሰያዩ ድርሳናት ታሪኮችና አሳቦች የተቀዱ?

ቁርአንን ስናነብ ብዙ መጽሐፍ ቅዱሰ ነክ ታሪኮችን እናገኛለን:: ሆኖም በመጽሐፍ ቅዱስ ከምናገኘው ታሪክ ጋር ያላቸው ስምምነት በጣም ውስን ነው:: በቁርአን የምናገኘው ብዙ ልዩነቶችንና ለውጦችን፣ እንዲሁም እንግዳ የሆኑ ታሪኮችን ጨምሮና አቅጣጫ ቀይሮ ይገኛል:: እነዚህ ታሪኮች ከቀደሙት መጻሕፍት ማለትም ከብሉይ ኪዳና ከሐዲስ ኪዳን ካልተገኙ ከየት ተገኙ?

እነዚህ በቁርአን የተገለጹት ከቀኖናዊው መጽሐፍ ቅዱስ የሌሉ ታሪኮች ምናልባት ቀኖናዊ ተቀባይነት ካልነበራቸው ከእስልምና በፊት ከነበሩ አዋልድ መጻሕፍት ታሪኮች ጋር ተመሳሳይት ይኖራቸው ይሆን? ብለን እንድንጠይቅ ያደርገናል:: እንዲህ ከሆነም እነዚህን አዋልድ መጻሕፍት ማግኘትና በቁርአን ላይ ካለው ታሪክ ጋር ማመሳከር ይኖርብናል::

በቁርአን ያሉትን ታሪኮች ልናስተያይባቸው የምንችላቸው ብዙ የአይሁድ አዋልድ መጻሕፍት (ብዙው ከታልሙድ ነው) አሉ:: እንዲህ ስናደርግ በእነዚህ ያሉት ታሪኮች፣ ሐተታዎችና ተረቶች ከቁርአን ጋር ብዙ ተመሳሳይነት ያላቸው ሆነው እናገኛቸዋለን::

የታልሙድ ድርሳናት በሁለተኛው መቶ ዓመት ከቃል ሕጎች (ሚሽናህ) እና ከእነዚያ ሕጎች ትውፊቶች (ጋማራ - Gamara) የተጠናቀሩ ነበሩ:: እነዚህ ሕግጋትና ትውፊቶች የተዘጋጁት የሙሴን ሕግ (ቶራህ - Torah) በየጊዜው ከሚለዋወጡ ነገሮች ጋር ለማስኬድ ነበር:: እንዲሁም የሕጉ ትርጓሜዎችና ማብራሪያዎች እንዲሁም ውይይቶች ነበሯቸው:: ነገር ግን የተጻፉበትን ዘመን ለማወቅ እንደ መስተዋትነት ይጠቀሙባቸው ነበር እንጂ ብዙዎች አይሁድ የታልሙድን ጽሑፎች አስገዳጅና ምስክር ወይም አስረጂ አድርገው አያዩዋቸውም::

እነዚህ ቀኖናዊ ያልሆኑ የአይሁድ አዋልድ ድርሳናት (ጽሑፎች) እንዴት የቁርአን አካል ሊሆኑ ቻሉ? በሰባተኛው መቶ ዓመት በዐረብ ምድር ብዙ አይሁዳውያን ነበሩ:: ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አስቀድሞ እንደተናገረው በ፸ ዓ.ም ኢየሩሳሌም በሮማውያን ስትጠፋ ከፍልስጥኤም ምድር የተሰደዱ ብዙ አይሁዳውያን ነበሩ:: የታልሙድ ታሪኮችና ሐተታዎች ከአባት ወደ ልጅ በቃል ይተላለፉ ነበር:: እያንዳንዱ ትውልድ ታሪኩንና ተረካውን በየራሱ መንገድ አንዳንዴም አካባቢያዊ ታሪኮችና ተረቶች እየተጨመሩበትና እየተሻሻለ ይተላለፍ ስለነበር የመጀመሪያው ታሪክ ምን እንደነበር በትክክል ለማወቅ አስቸጋሪ ነበር:: እነዚህ በታልሙድ ላይ ያሉ ነገሮች በመጀመሪያው የሙሴ ሕግ (በዐሥርቱ ትእዛዛት) ላይ ተጨምረዋል ብለው የሚያምኑ ጥቂት ጽንፈኛአይሁዳውያንም ነበሩ::

በሰባተኛው መቶ ዓመት መሐመድ ሲነሣ፣ በአንዳንዶች ምሁራን እምነት እነዚህን ታሪኮች አጠረቃቅሞ ቁርአን አደረጋቸው:: ስለሆነም ብዙ የአይሁዳውያን ትውፊቶችና አፈ ታሪኮች በመሐመድ ወይንም ምናልባት በኋላ በጸሐፊዎች ተቀባይነት አግኝተው የእስልምና ሃይማኖት አካል መሆናቸው አስገራሚ አይሆንም::

የእስልምናን ትውፊት የሚቀበሉ ደግሞ ከእነዚህ ታሪኮች ብዙዎቹ ለመሐመድ የደረሱት መዲና በነበሩት አይሁዳውያን ጓደኞቹ በኩል ነው ይላሉ:: የመሐመድ አጎት ዋራቃ የወንጌልን የተወሰነ ክፍል ወደ ዐረብኛ እንደተረጎመ፣ እንዲሁም ቡሀሪያ የተባለ ንስጥሮሳዊ መነኩሴ የመሐመድ የምስጢር መምህር እንደ ነበር ከእስልምና ትውፊት እንማራለን:: እንዲሁም የመሐመድ ሰባተኛ ሚስት ረሂማ እና ዘጠነኛ ሚስቱ ሳፊያ አይሁዳውያን ነበሩ:: ስምንተኛ ሚስቱ መርየም ደግሞ የመናፍቅ (የክርስትና) ቡድን ውስጥ ነበረች:: እነዚህ የብሉይና የሐዲስ ኪዳን ታሪኮችን የሚያውቁትንና የያዙትን ያህል ሳይነግሩት አልቀሩም:: እነዚህ ሚስቶቹ ቀኖናዊ (አሥራው) የሆኑትን የክርስትና መጻሕፍት ከአዋልዶቹ የለዩ ይሁኑ አሁይኑ አይታወቅም:: ነገር ግን ከአይሁዳውያን ታልሙድም ይሁን ከሌሎች የክርስትና አዋልድ መጻሕፍት ከቀኖናውያትም ይሁን ብቻ የሰሙትን እንዲሁ ሳይነግሩት አልቀሩም::

ሌላው ነገር ደግሞ በቁርአን የሚገኙት ብዙዎቹ ታሪኮች የኋላ ዘመን (ወደ ፯ኛው መቶ ዓመት ማብቂያ ወይም ከመሐመድ ሞት ከ፩፻-፩፻፶ ዓመት በኋላ) ናቸው፡፡ ምናልባትም ከራሳቸው የቃል ታሪኮችና ከአይሁዳውያን ታልሙድ፣ የተዋሷቸውን ታሪኮች በመውሰድ በፋርሳውያን ወይም በሶርያውያን ጸሐፊዎች የተጻፉ ይመስላሉ፡፡ ታሪኮቹን ወደ ኋላ በመውሰድ በሰባተኛው መቶ ዓመት በነበረው በመሐመድ ሰብእና ላይ አሳረፏቸው፡፡

ከእነዚህም የተወሰኑትን በተለይም ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር የሚመሳሰሉትን ታሪኮች ወስደን ከዚያ በፊት ከነበሩት ድርሳናት ጋር እናስተያያቸው፡፡

## ፩. የሰይጣን ለአዳም አለመስገድ

ሱራ ፪:፴፬፣ ፲፯:፷፩ እና ፯:፲፩-፲፫ ላይ ሰይጣን ለአዳም አልሰግድም ማለቱ ተጽፏል፡፡

«...ከዚያ ለመላእክቶች ለአዳም ስገዱ አልን፣ ወዲያውም ሰገዱ፣ ኢብሊስ (ዲያብሎስ) ሲቀር ከሰጋጆች አልሆነም፡፡ (አላህ) ባዘዝኩህ ጊዜ ከመስገድ ምን ከለከለህ? አለው፣ እኔ ከርሱ የበለጥኩ ነኝ፣ ከእሳት ፈጠርከኝ፣ እርሱን ግን ከጭቃ ፈጠርከው አለ፡፡ ከርሷ (ከገነት) ውረድ፣ በርሷ ውስጥ ልትኮራ አይገባህምና ውጣም አንተ ከወራዶቹ ነህና አለው፡፡» ሱራ ፯:፲፩-፲፫

በክርስትና ትምህርት ሰይጣን የወደቀው ለአዳም አልሰግድም በማለቱ አይደለም፡፡ እንዲሁም ዲያብሎስ የወደቀው ከአዳም መፈጠር በፊት ነው፡፡

ይህ ታሪክ ከሁለተኛው መቶ ዓመት ታልሙድ ይገኛል፡፡

## ፪. ቃየንና አቤል

ሱራ.፭:፳፯-፴፪ ያለው የአቤልና የቃየን ታሪክ ጥሩ ምሳሌ ነው፡፡ ታሪኩ በመጽሐፍ ቅዱስ እንዳለው ታሪክ ቃየን ወንድሙን አቤልን ሲገድለው ይጀምራል (በቁርአን በስማቸው ባይጠቀሱም)፡፡ ሆኖም በአያ ፴፩ ላይ ቃየን ወንድሙን አቤልን ከገደለው በኋላ ታሪኩ በመጽሐፍ ቅዱስ ካለው ይለያል፡፡ እንዲህ ይላል፡-

«ያን ጊዜም የወንድሙን ሬሳ እንዴት እንደሚሸሽግ ያሳየው ዘንድ አላህ መሬትን የሚጭር ቁራን ላከለት፣ ወይ እኔ የወንድሜን ሬሳ እሸሽግ ዘንድ እንደዚህ ቁራ መሆን አቃተኝን? አለ፣ ከጸጸተኞችም ኾነ፡፡»

*የዮናታን ቤን ኦዝያ ታርገም /Targum/ ደግሞ እንዲህ ይላል፡-*

«አዳምና ሔዋን በአስከሬኑ አጠገብ ተቀምጠው ምን እንደሚያደርጉ ጨንቋቸው ያለቅሱ ነበር፣ ከዚያ በፊት ስለመቅበር የሚያውቁት ነገር አልነበረምና፡፡ ያን ጊዜም ቁራ መጣና የሌላ የሞተ ቁራ በድን ወስዶ መሬቱን ቆፈረና እነርሱ እያዩት በዓይናቸው ፊት ቀበረው፡፡ አዳ ምም የቁራውን ምሳሌ እንከተል አለ፡፡ የአቤልን ሰውነት ወስዶ ወዲያውኑ ቀበረው፡፡»

እገሌ አገሌን ቀበረ ከሚለው ውጭ፣ ሁለቱ ታሪኮች ተመሳሳይ ናቸው፡፡ ስለሆነም መሐ መድ ወይም ሌላው የኋላ ዘመን ጸሐፊ ይህን ታሪክ ያገኘው ከዚህ የአይሁድ ታልሙድ ነው ብለን መደምደም እንችላለን፡፡ የአይሁድ ታሪክ በቁርአን ላይ መሠረታዊ ዶግማ ተደ ርጎ ከ «ሰማይ የወረደው» መጽሐፍ ክፍል ሆኖ እናገኘዋለን፡፡

ይህ ብቻ አይደለም፣ ሱራ ፭ን ማንበብስንቀጥል አያ ፴፪ ላይ ከሌላ የአይሁድ ታል ሙድ የተቀዳ እናገኛለን፡፡

*ቁርአን ሱራ ፭:፴፪:-*

«በዚህ ምክንያት በእስራኤል ልጆች ላይ እነሆ ያለ ነፍስ (መግደል) ወይም በምድር ላይ ያለማጥፋት ነፍስን የገደለ ሰው ሰዎቹን ሁሉ እንደገደለ ነው፣ ሕያው ያደረጋትም ሰው ሰዎቹን ሁሉ ሕያው እንዳደረገ ነው ማለትን ጻፍን...»

*ሚሽናህ ሳንሄድሪን ፬:፭*

«ወንድሙን በገደለው በአቤል ላይ እንዲህ ተብሎ እናገኛለን፡- የወንድምህ ደም ከም ድር ይጮኻል (ይህ ከመጽሐፍ ቅዱስ ኦሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ ፬ ቁጥር ፲ ላይ የተጠቀሰ ነው) እንዲሁም እንዲህ አለ፡- በአንድ ሰው ብቻ ደም አለበት ያለ አይደለም፣ ብዙዎች ደሞች አሉበት አለ እንጂ፡፡ አንድን ሰው የገደለ የሰውን ዘር በሙሉ እንደገደለ ያሳይህ ዘንድ

አንድ ሆነህ ተፈጠርህ፤ የአንድን ሰው ሕይወት ለታደገ ደግሞ የሰውን ዘር በሙሉ እንዳዳነ ይቆጠርለታል::»

በፊተኛው አያ (፴፩) እና በሚከተለውና ከላይ ባነበብነው አያ (፴፪) መካከል ግንኙነት የላቸውም:: የአቤል በቃየን መገደል ከሰው ልጅ ዘር መገደልና መዳን ጋር ግንኙነቱ ምንድን ነው? ምንም ዓይነት አመክንዮአዊ ግንኙነት የላቸውም:: ይህ አያ እንዲያውም የሰውን ልጅ ሁሉ ኃጢአት ሊሸከም ይመጣል ተብሎ በብሉይ ኪዳን ዘመን በተስፋ ሲጠበቅ ለነበረው የክርስቶስ የማዳን ሥራ ደጋፊ ነው:: (ዮሐ.፩÷፳፱) ሆኖም ከሚቀድመው አያ አሳብ ጋር አብሮ አይሄድም::

ወደ አይሁድ ታልሙድ ስንመለስ ይህንን በሚሽናህ ሳንሄድሪን ምዕራፍ ፬ ቁ. ፭ ላይ ከላይ የተጻፈውን እናገኛለን:: በዚህም ጸሐፊው ከየት እንዳገኘውና ለምን እዚህ ላይ እንደ ጨመረው እንረዳለን:: በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ባለ ኃይለ ቃል ላይ የተሰጠ የአንድ ረቢ አስተያየትና ትርጓሜ በቁርአን በሱራ ፭:፴፪ ላይ ቃል በቃል ተደግሟል:: የአንድ ረቢ አስተያየት እንዴት የቁርአን አካል ሆኖ የአላህ ነው ተባለ? አላህ የሆነ ነገር ከረበናት ይማራል ማለት ነው? ወይስ መሐመድ ወይም የኋላ ጸሐፍያን ይህንን ተግሣፅ ከዚህ ረቢ ጽሑፍ ቀዱት?

የሁለቱን ታሪኮች ግንኙነት የምናገኘው የሳንሄድሪንን ሚሽናህ ስናነብ ብቻ ነው፡ በቁርአን ላይ በሁለቱ (በ፴፩ እና ፴፪) መካከል የአሳብ ፍሰት ወይም ግንኙነት ያለመኖሩን ምክንያት አሁን ለመረዳት ቀላል ነው:: የሱራ ፭ ጸሐፊ ረቢው የሚናገርበትን ጥንተ ታሪክና የጆርባ ጉዳይ አልተረዳውም:: ስለዚህም እነዚህ የአንድ ግለሰብ ረቢ አስተያየቶችና ሐተታዎች እንጂ የመጽሐፍ ቅዱስ ቃላት አለመሆናቸውን ስላላወቀ የሰማውን ነገር አንድምታውንና ምልከታውን ሳይረዳ እንዲሁ ቁርአን ላይ ጨመረው::

በሱራ ፳፭:፬-፭ ላይ የኩረሻ (ግልበጣ) ክስ በእርሱ ባላመኑ የመዲና ሰዎች በመሐመድ ላይ የቀረበበት ያለ ምክንያት እንዳልሆነ እናያለን:: ክሱ እንዲህ ይላል:-

«ያላመኑት ግን ይህ (ቁርአን) መሐመድ የፈጠረውና ሌሎችም ሕዝቦች የረዱት ውሸት ነው  እንጂ ሌላ አይደለም ይላሉ:: በእውነትም በደልንና ሐሰትን ሠሩ:: እንዲህም አሉ:- እንዲጻፍ ያደረገው የቀደሙ ሰዎችን ተረቶች ነው:: በቀንና በማታም በቃሉ እየተናገረ ያጽፋቸዋል::»

ይህ በዘመኑ የነበሩና መሐመድን በደምብ የሚያውቁት የነበሩት የመዲና ሰዎች ክስ፤ ብዙ እስላሞች ለማመን ከሚፈልጉት ነገር ይልቅ ወደ እውነቱ የቀረበ ነው:: በመሐመድም ሆነ በኋለኞቹ ጸሐፊዎች ያላመኑት የመዲና ሰዎች እነዚህን ከሰማይ የወረዱ ናቸው፤ የሚባሉትን ታሪኮች ምንጮች ስላወቁ ነው:: በዚያ አካባቢ ይኖሩ ከነበሩት አይሁዶች ብቻ ሳይሆን ከአካባቢው አገሮች ወደ መካና ወደ ተለያዩ የዐረብ የንግድ ከተሞች ይመጡ ከነበሩት አይሁዶች እነዚህን ተረቶችና አፈ ታሪኮች ይሰሟቸው ስለነበር የሚያውቋቸውን አፈ ታሪኮችና ሐተታዎች «ከሰማይ የወረዱ ናቸው» ሲባሉ ሊያምኑ አልቻሉም::

## ፫. አብርሃም

ሱራ ፳፩:፶፩-፸፩ ላይ የአብርሃምን ታሪክ እናገኛለን (ብዙ ስለሆነ እዚህ ላይ አልተጻፈም):: አብርሃም ሕዝቡን ስለ ጣዖት አምልኳቸው ከተከራከራቸው በኋላ አንድ ታላቅ ጣዖት ብቻ ሲቀር ሌሎቹን ሰባበራቸው:: ሕዝቡም ይህን ሲያዩ አብርሃምን ጠርተው ይህን ያደረገው እርሱ እንደሆነ ጠየቁት:: እርሱም ታላቁ ጣዖት ይህን ሠራ አላቸው:: ይናገርም እንደሆነ ትልቁን ጣዖት ጠይቁት አላቸው፡ እነርሱም እነዚህ የሚናገሩ መሆናቸውን በርግጥ አውቀሃል አሉት:: ከአላህ ሌላ ለምን ትገዛላችሁ? ባላቸው ጊዜ በእሳት ላይ ጣሉት:: አላህም እሳቱን በአብርሃም ላይ ቀዘቃዛ ሁኚ አላት:: ከእሳቱም በተአምራት ሳይቃጠል በደኅና ወጣ ይላል::

ይህ ታሪክ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አይገኝም:: ሆኖም ሚድራሽ ራባህ በሚባል የሁለተኛው መቶ ዓመት የአይሁድ ታልሙድ ይገኛል:: በዚህ የራባህ ሚድራሽ ላይ አብርሃም ከሁሉም ታላቅ ከሆነው በቀር ሌሎቹን ጣዖታት ይሰብራቸዋል:: አባቱና ሌሎቹም ሰዎች በዚህ ምክንያት ይጠይቁታል፤ እርሱም በቁርአን ላይ ካልተጻፈ ቀልድ ቢጤ ጋር በታላቁ

ጣዖት ፊት ለታናናሾቹ ጣዖታት ይበሉ ዘንድ በሬን እንደሰጣቸውና እነርሱም ስለበሉ አላከ በሩትም፤ ስለዚህም ታላቁ ጣዖት ትንንሾቹን ጣዖታት አጠፋቸው፡፡ የተቆጣው አባቱ አብርሃም የተናገረውን አላመነውም፤ ስለሆነም ናምሩድ ወደሚባል ሰው ወሰደው፤ እርሱም ወደ እሳት ጣለው፡፡ እግዚአብሔር እሳቱን ውኃ አደረገለት፣ ያለ ምንም ጉዳት በደኅና ወጣ ይላል፡፡

የሁለቱ ታሪኮች ተመሳሳይነት አሌ የማይባል ነው፡፡ የሁለተኛው መቶ ዓመት የአይሁድ አፈ ታሪክ በ«ቅዱስ ቁርአን» ላይ ተደግሟል፡፡ መሐመድ ወይም ሌላ ጸሐፊ ይህን ታሪክ ከአይሁድ ሰምቶ ነገር ግን የመጽሐፍ ቅዱስ ቅንጥብጣቢ ታሪኮችን ከአይሁዳውያን ወዳጆቹና ከሚስቶቹ ቢሰማም መጻሕፍታቸውን ስላላነበበ ከአንድ ዓይነት ምንጭ የመጣ መሰለው፡፡ በዚህም የአይሁድን አፈ ታሪክ በቁርአን ውስጥ አሰፈረ፡፡

## ፬. ሰሎሞንና ንግሥተ ሳባ

በሱራ ፳፯:፲፯-፵፬ ላይ የሰሎሞንን ታሪክ፣ የሁድሁድን (የዝናብ ወፍን) ታሪክና የንግሥተ ሳባን ታሪክ እናገኛለን፡፡ በቁርአን የተጻፈውን የሰሎሞንን ታሪክ ካነበብን በኋላ ከቁርአን መፈጠር በፊት አምስት መቶ ዓመት ቀድሞ በሁለተኛው መቶ ዓመት በተጻፈው የአይሁድ የታሪክ መጽሐፍ ከአስቴር ታርገም ፪ ላይ ካለው ጋር ማነጻጸር ጠቃሚ ነው፡፡

*ቁራን፣ ሱራ ፳፯:፲፯-፵፬*

*«ለሰሎሞንም ሠራዊቶቹ ከጅን (ከጋኔን) ከሰውም ከበራሪም የሆኑት ተሰበሰቡ፤ እነሱም በየደረጃቸውና በየማዕረጋቸው ነበሩ፡፡» ፲፯*

*«በራሪዎቹንም ተመለከተ፤ ዓለም፡- ሁድሁድን (የዝናም ወፍን) ለምን አላየውም! በውነት ከራቁት ነበርን? ላልተገኘበት ምክንያት በቂ ማስረጃ ካላቀረበልኝ በስተቀር በብርቱ ቅጣት እቀጣዋለሁ ወይም እገድለዋሁ አለ፡፡ ወፉም ሩቅ ያልሆነ ጊዜ ዘገየ፤ (መጥቶም) አለ፡- አንተ ያልገዛኸውን አገርና ድንበር አይቼ መጣሁ፤ ከሳባ እውነተኛ ወሬን ይዤልህ መጥቻለሁ፡፡ (በዚያም) የምትገዛቸውን ሴት አገኘሁ፣ በሁሉም ነገር የተሰጣት ናት፣ አስደናቂ ዙፋንም አላት... አለ፡፡ » ፳-፳፩*

*«ሰሎሞንም አለ፡- እውነት ተናግረህም ይሁን ዋሽተህ መሆኑን ወደፊት እናያለን አለ፡፡ ይህንን ደብዳቤዬን ይዘህ ሂድ፤ ወደነርሱም ጣለው፤ ከዚያም ከነሱ ዘወር በል፤ ምን እንደሚመልሱም ተመልከት፡፡ (እርሷም በደረሳት ጊዜ) አለች፡- እላንተ መማክርቶች ሆይ! ክብር ያለው ጽሑፍ ወደኔ ተጣለ፤ እርሱም ከሰሎሞን ነው፤ በአላህ ስም እጅግ በጣም ርኅሩህ በጣም አዛኝ በሆነው፤ በኔ ላይ አትኩሩ ታዛዦችም ሆናችሁ ወደኔ ኑ (የሚል ነው)፡፡ እናንተ መማክርቶች ሆይ! በነገሬ የሚበጀውን ንገሩኝ፤ እናንተ ሳትገኙ ምንም ነገር ወስኜ አላውቅምና አለች፡፡ እነርሱም፣ እኛ የኃይል ባለቤቶች የብርቱ ጦርም ባለቤቶች ነን፤ ግን ትእዛዙ ወደ አንቺ ነው፤ ምን እንደምታዝርም አስተውይ አሏት፡፡ » ፳፪-፴፫*

*«እኔም ወደነሱ ገጸ በረከትን የምልክና መልክተኞቹ በምን እንደሚመለሱ የምፎባበቅ ነኝ አለች፡፡» ፴፭*

*«በመጣችም ጊዜ፡- ...» ፵፪*

*«ወደ ታላቁ ቤተ መንግሥት እንድትገባ ተጠየቀች፡፡ እርሷ ግን ባየቺው ጊዜ ባህር ነው ብላ ጠረጠረች፤ ልብሷን ወደ ላይ ወደ ባቶቿ ከፍ አደረገች፡፡ እርሱ ግን ከመስተዋት የለሰለሰ ሕንፃ ነው አላት...» ፵፬*

*የአስቴር ታርገም ፪*

*«ሰሎሞን ትእዛዝ ሰጠ፣ ንጉሥና ከጂኒ፣ ከምድር አራዊትና ከሰማይ አዕዋፋት የሆኑ ሠራዊቶችን እልክብሃለሁ የሚል፡፡ ያን ጊዜም ያ ወፍ ራሱን እያዝናና ሊገኝ አልቻለም፡፡ ንጉሥ ሰሎሞንም ወፉን በኃይል ይዘው እንዲያመጡት አዘዘ፤ በርግጥም ሊገድለው ፈልጎ ነበር፡፡*

*ነገር ግን ወዲያውኑ ወፉ ንጉሡ ባለበት መጣና እንዲህ አለ፡- ጌታዬ ንጉሥ ሆይ፣ ዓለሙን ሁሉ አየሁት፤ አንተ የማትገዛውን የሳባን ግዛትና ከተማም አየሁት፡፡ የሳባ ንግሥት በምትባል ሴት ይመራል፡፡ እንዲሁም በምሥራቅ (ሳባ) ያለውን የተመሸገ ከተማ አገኘሁት፤ በዙሪያውም የብርና የወርቅ ድንጋይ በየጎዳናው አለ፡፡*

*«ባጋጣሚ የሳባ ንግሥት ባሕር ልታመልክ በጧት ወጥታ ነበር:: ጸሐፊዎቹ ደብዳቤ አዘጋጅተው በወፉ ክንፍ ላይ አደረጉት፤ ወፉም መልእክቱን ይዞ ከሳባ ምሽግ ደረሰ:: በወፉ ክንፍ ያለውን ደብዳቤ አይታ (ሳባ) ከፍታ አነበበችው::*

*«ንጉሥ ሰሎሞን ሰላምታውን ያቀርባል:: ወደኔ መምጣትና የእኔን ልግስናና ባለጸግነት መጠየቅ ደስ ቢያሰኝሽ ከሁሉም በላይ ከፍ ከፍ አደርግሻለሁ:: ይህ ደስ የማያሰኝሽ ከሆነ ግን ነገሥታትንና ሠራዊቶችን እልክብሻለሁ:: የሳባ ንግሥት ይህን በሰማች ጊዜ ልብሷን ቀደደች፤ ወደ መማክርቶቿም ልካ ምን ባደርግ ይሻለኛል? አለቻቸው:: ሰሎሞንን አያውቁትም፤ ሆኖም ውብ ጌጣጌጦችንና የከበሩ ድንጋዮችን የተመሉ መርከቦችን በባሕር እንድትልክና መልእክ ትም አብራ እንድትልክ መከሯት::*

*በመጨረሻም በመጣች ጊዜ ሰሎሞን ይቀበላት ዘንድ መልእክተኛ ላከ ... መምጣቷን ሲሰማም በመስታወቱ ቤተ መንግሥት ተነሥቶ ተቀመጠ:: የሳባ ንግሥት ባየችው ጊዜ የመስታወቱ ወለል ውኃ መሰላት፤ ስለሆነም በዚያ ላይ ስትራመድ ልብሷን ከፍ አደረገች:: ሰሎሞን በእግሯ ላይ ያለውን ጠጉር ባየ ጊዜ እንዲህ ብሎ ወደሷ ጮኸ...»*

ሁለቱንም ካነበብን በኋላ የሰሎሞንንና የሳባን ንግሥት ታሪክ በቁርአን ላይ የጻፈው ሰው ይህን ታሪክ ከየት እንዳገኘው ግልጽ ነው:: ሁለቱ ታሪኮች አንድ ዓይነት ናቸው:: ጅኖቹ፣ ወፎቹ፣ በተለይም ደግሞ የጠፋውና በኋላ የሳባን ንግሥት ጉዳይ፤ እንደ መታረቂያ አድርጎ ያቀረበውና መልክተኛው ወፍ፣ መልእክቱ፣ የመስታወቱ ውኃ መምሰል፤ ሁሉም የእነ ዚህ ሁለት ታሪኮች ልዩ የሆኑ የጋራ ገጽዞቻቸው ናቸው:: እነዚህ ታሪኮች እንዲሁ ባጋጣሚ ተመ ሳሰለው ይሆን? ይህ ታሪክ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የለም::

## ፰. ስለ ኢየሱስ ልደትና በሕፃንነት ዘመኑ ስላደረጋቸው የተለያዩ ድርጊቶች የሚናገሩ አንቀጾች

እነዚህ ነገሮች ቤተ ክርስቲያን «ቀኖናውያን» አድርጋ በተቀበለቻቸው መጻሕፍት ማለ ትም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሌሉ ሲሆን፤ የሚገኙት በወንጌል ስም ተጽፈው ይሰ ራጩ በነበሩ የተለያዩ የሁለተኛው መቶ ዓመት አዋልድ መጻሕፍት ነው:: ከእነዚህ ታሪ ኮች ለምሳሌ ያህል የሚከተሉትን እንመልከት::

*ሀ/ የዘንባባው ዛፍ*

ሱራ ፲፱:፳፪-፳፮ ላይ ስለ ማርያም፣ ስለ ሕጻኑ ኢየሱስ፣ ስለ ዘንባባ ዛፍና ከሥሩ ስለ ሚፈልቀው ምንጭ እናነባለን::

*«እርሱን (ኢየሱስን) ፀነሰችው፤ በሆድዋም ይዛው ወደ ሩቅ ስፍራ ገለል አለች:: ምጡም ወደ ዘንባባይቱ ግንድ አስጠጋት:: ዋ! ምነው ከዚህ በፊት በሞትኩ፤ ተረስቼም የቀረኹ በሆንኩ አለች:: ከበታቿም እንዲህ ሲል ጠራት:- አትዘኚ፤ ጌታሽ ከበታችሽ ትንሽን ወንዝ በእርግጥ አድርጓል:: ዘንባባይቱንም ግንድ ወዳንቺ ወዝውዣት፤ ባንቺ ላይ የበሰለን የተምር እሸት ታረግፍልሻለችና:: ብይም ጠጪም፤ ተደሰቺም»* ፲፱:፳፪-፳፮

ይህ ታሪክ በመጽሐፍ ቅዱስ የለም:: ይህ ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ የተገኘው በሁለተ ኛው መቶ ዓመት ይሠራጭ በነበረ አንድ አዋልድ መጽሐፍ ላይ ነው:: እርሱም እንዲህ ይላል:-

*«ማርያም በበረሃው ቃጠሎ ከደከመች ከሦስት ቀን በኋላ ከዘንባባ ዛፍ ሥር ትንሽ ታርፍ ዘንድ ዮሴፍን ጠየቀችው:: ዛፉ ብዙ ፍሬ ተሸክሞ ባየችው ጊዜ ከዚህ ፍሬ ትንሽ ብናገኝ ጥሩ ነበር አለች:: ያን ጊዜ ሕፃኑ ኢየሱስ ፈገግ እያለ ወደ ላይ ተመለከተና የዘንባባውን ዛፍ < ትንሽ ፍሬ ወደ ታች ጣል> አለው:: ወዲያውኑ ዛፉ ወደ እርሷ አዘነበለ፤ እነርሱም በሉ:: ያን ጊዜም ኢየሱስ እንዲህ አለ:- <ዘንባባ ሆይ፣ ተነሥ፣ በገነት ካሉት የአባቴ ዛፎች አንዱ ሁን፤ ግን በሥሮችህ ከበታችህ ያለውን ምንጭ ክፈትና ከበታቹ ከሚፈሰው ውኃ አምጣ::>* (The Lost Books of the Bible, New York, Bell Publishing Co., p. 38)

*ለ/ ከጭቃ ወፎችን ስለ መፍጠር*

በሱራ ፫:፵፱ ላይ ሕፃኑ ኢየሱስ ከጭቃ የወፍ ቅርጽ እንደሠራና እስትንፋሱን እፍ ሲልበት ወፍ እንደሚሆን ይናገራል::

*«ወደ እስራኤል ልጆች መልክተኛ ያደርገዋል (ኢየሱስን)፤ ይላልም:- ከጌታችሁ ዘንድ በምል ክትና በተአምር መጣኋችሁ:: እኔ ለእናንተ ከጭቃ እንደ ወፍ ቅርጽ እፈጥራለሁ፤ በርሱም እተነፍስበታለሁ፤ በአላህም ፈቃድ ወፍ ይሆናል::»* ፫:፵፱

ይህ የሚገኘው ቤተ ክርስቲያን ሃይማኖትን ለመግለጥና ለማስተማር እንዲሁም ለምስክርነት ቀኖናዊ አድርጋ በተቀበለቻቸው በዐራቱ ወንጌሎች አንጻር ግኖስቲኮች እየጻፉ በሐዋርያት ስም እየሰየሙ ያሰራጯቸው ከነበሩት አስመሳይ ወንጌሎች በአንዱ ነው:: ይህ ታሪክ የሚገኘው *«ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ የሕፃንነት ዘመን የሚናገር የቶማስ ወንጌል»* ከተባለ መጽሐፍ ነው:: ይህ መጽሐፍ ይህን በተመለከተ እንዲህ ይላል:-

*«ያን ጊዜም ትንሽ ጭቃ ወሰደ፤ ከርሱም ዐሥራ ሁለት ወፎችን ሠራ ... ኢየሱስም እጆቹን አንድ ላይ አድርጐ አጨበጨበና ወፎቹን <ሂዱ፣ ብረሩ> አላቸው::»*

ይህን የመሰሉ ከተለያዩ የግኖስቲኮች «መስመ ወንጌሎች» /Pseudo gospels/ እና ከክርስቲያኖች ቀኖናውያት ሳይሆን አዋልድ መጻሕፍት የተቀዱ ብዙ ታሪኮች ይገኛሉ:: እዚህ ላይ ዋናው ነገር ጌታችን ወፍ ከጭቃ የመፍጠሩ ጉዳይ ወይም በሕፃንነቱ የመናገሩ ጉዳይ አይደለም:: እርሱ የባሕርይ አምላክ እንደመሆኑ ማንኛውንም ነገር ማድረግ አይሳነውምና:: ቁርአን እንደሚባልለት «ከሰማይ የወረደ» ሳይሆን እንደ ልመና ጥሬ ከተለያዩ ድርሳናት የተጠረቃቀመ መሆኑን ግን ያሳየናል:: ከአዋልድ መጻሕፍት የሰሟቸውንና ከቀኖናውያት መጻሕፍት ያለውን ያልለዩ ሰዎች የነገሩትን ሳያጣራና የትኞቹ ታሪኮች ከቀኖናውያት (አሥራው) መጻሕፍት እንደተገኙ፤ የትኞቹ ደግሞ ከአዋልድ እንደ ተገኙ ስላላወቀ የተገኘውን ሁሉ አጠራቅሞ አንድ መጽሐፍ አደረገው::

በቁርአን ውስጥ የእርስ በርስ ግጭትና መዘበራረቅ ያስከተለው ዋናው ምክንያትም ይኸው ነው:: ከክርስትና የተገኙትንና ከግኖስቲኮች የተቀዱትን፣ ከቀኖናውያት መጻሕፍት የተቀዱትና ከአዋልድ የተቀዱት ሊገጣጠሙ አልቻሉም:: ከዚህ አጣብቂኝ ለመውጣት የሚጋጭ የቁርአን ቃልና አንቀጽ ሁሉ በሌላ የተተካ ወይም የተሻረ ነው በሚል ለማምለጥ ቢሞክሩም የሚያስኬድ አልሆነም:: ከዚህ የምንማረው ሌላው ነገር ክርስቲያኖችም ቀኖናዊ በሆኑት መጻሕፍት ማለትም በመጽሐፍ ቅዱስና ታሪክ ለማወቅ፣ ለግል ምክርና ለመሳሰለው የተጻፉ አዋልድ መጻሕፍትን በሚገባ መለየትና በአግባቡ መጠቀም የሚያስፈልግ መሆኑን ነው:: ቀኖናውያት መጻሕፍትን ከአይሁድ ታልሙድና በዘመኑ ከነበሩ የተለዩ የአዋልድ ድርሳናት፣ እንዲሁም ከግኖስቲኮች የፈጠራ ወንጌሎች የደባለቁ ሰዎች መሐመድን የተደባለቀ ታሪክ በመንገር በቁርአን ላይ ላለው ችግር የራሳቸው ዓይነተኛ ሚና ነበራቸው::

## ፮. «ኢየሱስ ክርስቶስ አልተሰቀለም» የሚሉት ታሪክ የትመጣ

*ሱራ ፬፻፶፯-፬፻፶፰* እንዲህ ይላል:-

*«እኛ የአላህን መልክተኛ የመርየምን ልጅ አልመሲ ዒሳን ገደልን በማለታቸው (ረገምናቸው)፤ አልገደሉትም፤ አልሰቀሉትም፤ ግን ለእሱ (የተገደለ ሰው በዒሳ) ተመሰለ፤ እነዚያም በርሱ ነገር የተለያዩት ከርሱ (መገደል) በመጠራጠር ውስጥ ናቸው፤ ጥርጣሬን ከመከተል በስተቀር በርሱ ነገር ምንም እውቀት የላቸውም፤ በርግጥም አልገደሉትም::»*

## መሐመድ ይህንን የሰውን ሁሉ ድኅነት ከንቱ የሚያደርግ ተረት መሰል ነገር ከየት አገኘው?

መሐመድ ስለ ክርስቶስ መሰቀልና መሞት ጉዳይ የሰማው የግኖስቲኮች ተጽእኖ ከለከፋቸው ወይም ከራሳቸው ከግኖስቲኮች መሆኑ ግልጽ ሆኖ የሚታየው በዚህ ነው:: ግኖስቲሲዝም የግሪኮችን ፍልስፍናና ክርስትናን ለመደባለቅና ከሁለቱ አንድ ዓይነት አዲስ ሥርዓተ እምነት ለመፍጠር ይደረግ የነበረ የመናፍቃን ሙከራ ነበር:: ግኖስቲኮች ምንታዌ (ሁለት) በሆኑ በብርሃንና በጨለማ መንግሥታት ያምኑ ነበር:: መንፈሳዊ የሆነው ሁሉ ለምሳሌም የሰው ነፍስና መንፈስ የብርሃን መንግሥት ገንዘቦች ሲሆኑ፤ ቁስ አካል የሆነ ሁሉ፣ የሰውን አካል ጨምሮ የጨለማው መንግሥት ግዛት ነው ብለው ያምኑ ነበር:: የብርሃኑ ዓለም

የተፈጠረው በደጉ አምላክ ሲሆን፤ ክፉው አምላክ ደግሞ የጨለማውን ዓለም ፈጠረ ይላሉ:: ይህ አስተሳሰባቸውም ቁስ አካላዊ የሆነ ሁሉ፣ የሰውን ሥጋ ጭምር ኃጢአት ስለሆነ «ኢየሱስም የእኛን ሥጋ አልተዋሐደም፣ እንደኛም ሰው አልሆነም» ወደሚል የለየለት ክህደት ወሰዳቸው:: «ሰው የሆነና ሥጋ የለበሰ መሰለ እንጂ በእውነት ሰው አልሆነም» አሉ:: የግኖስቲኮች ትምህርት ውጥንቅጡ የወጣና የተዘበራረቀ የነበረ ሲሆን፤ ብዙዎቹ ኢየሱስ በመስቀል ላይ አልሞተም ይሉ ነበር:: ብዙ ግኖስቲኮች ለምሳሌም በእስክንድርያ ከ፻፳-፻፵ ዓም. ድረስ የኑፋቄ ትምህርቱን ይነዛ የነበረው ባስሊደስ የተባለው ግኖስቲክ ኢየሱስ በመስቀል ላይ አልሞተም ብሎ እስከ መካድ ደርሷል::

*ባሲሊደስም እንዲህ ያስተምር ነበር:-*

*«...ያልተወለደው አባት የሰውን ውርደት ባየ ጊዜ ክርስቶስ የተባለውን ላከው ... በምድር ላይ ላሉ ሰዎችም ተአምራትን የሚያደርግ ሰው ሆኖ ታያቸው:: ስለዚህ በመስቀል ላይ መከራ አልተቀበለም፤ ነገር ግን መስቀሉን እንዲሸከምለት ግድ የተባለው ከቀሬና የሆነ ስምዖን የሚባል ሰው እንጂ እርሱ አልተሰቀለም:: እርሱ (ስምዖን) ኢየሱስ ነው ተብሎ ይታመን ዘንድ በክርስቶስ ስለተለወጠ ካለማወቅና ከመሳሳት የተነሣ እርሱ (ስምዖን) ተሰቀለ:: ነገር ግን ኢየሱስ ራሱ የስምዖንን ገጽታና እይታ ገንዘብ አደረገ፤ በጎንም ሆኖ በሕዝቡና በዙሪያው ባሉት ላይ በመቀለድ ሳቀባቸው:: ... ስለዚህ የተሰቀለውን ማመን ለማንም አያስፈልገውም፤ በሰው ምሳሌ የመጣውንና የተሰቀለ የመሰለውን ኢየሱስ የሚባለውን እንጂ..»* (*Jesus till Moder Teresa, Tergel, Verbum, 1973, p. 29*)

## የተሻሩ የቁርአን ሕጎችና አንቀጾች

በቁርአን ላይ የተሻሩ፣ የተለወጡና የተተኩ ብዙ አንቀጾችና ሕጎች አሉ:: በአንድ በኩል የአላህ ቃል እንደማይለወጥ ይናገራል:: ለምሳሌም:-

*«የአላህን ቃላት መለወጥ የላትም»* ይላል:: ሱራ ፲:፷፬፤ ፮:፻፲፭:: ከዚህም የበለጠ ጠንካራ ዐዋጅ በሱራ ፬:፹፪ ላይ እንዲህ ይላል:- *«ቁርአንን አያስተነትኑምን? ከአላህ ሌላ ዘንድ በነበረ ኖሮ በርሱ ውስጥ ብዙ የሆነ መለያየትን ባገኙበት ነበር::»* በቁርአን ውስጥ ያለውን እርስ በርስ መቃረንና መጣላት የሙስሊም ምሁራን ፊት /ቀድመው/ የተሰጡ አንዳንድ ትእዛዞች በኋላ በተገለጡ ትእዛዞች የተሻሩ መሆናቸውን በመግለጽ ለማብራራት ይሞክራሉ:: የሚጋጩትንና እርስ በርሳቸው የሚቃረኑትን የቁርአን አንቀጾችና ቃላት «ተሻሽለዋል» ወይም «ተለውጠዋል» በሚል መንገድ ችግሩን ለመፍታት ይሞክራሉ:: ሆኖም ግን ቁርአን የተጻፈው በሱራዎቹ የታሪክ ወይም መገለጥ ቅደም ተከተል ሳይሆን፤ ሱራዎቹ በያዙት አንቀጽ (አያ) ብዛት ቅደም ተከተል ስለሆነ የትኛው ፊት፣ የትኛው ወደኋላ እንደተገለጸና የትኛው የሚጋጭ አንቀጽ፤ በየትኛው እንደተለወጠና እንደተተካ ማወቅ አይቻልም:: እንዲሁም በእስልምና ትውፊት መሠረት ብዙዎቹ ሱራዎች ለመሐመድ በአንድ ጥራዝ አልተሰጡትም:: ስለሆነም በአንድ ሱራ ውስጥ የቀደሙ እንዲሁም የኋላ የሆኑ አያዎች ተደባልቀው ይገኛሉ:: ታዲያ የትኞቹ የበለጠ ተሰሚዎች ወይንም ከነርሱ በፊት የነበረውን የተኩ እንደሆኑ ማወቅ ይቻላል?

የመለወጥ ሕግ በሱራ ፪:፩፻፮ና ፩፻፰ ላይ ተገልጾአል:: *«ከአንቀጽ ብንለውጥ ወይም እርሷን ብናስረሳህ ከርሷ የሚበልጥን ወይም ቢጤዋን እናመጣለን»* ይላል:: ሱራ ፲፯:፹፮፣ ፲፮:፩፻፩፣ እንዲሁ መለወጥ ያለውን በተሻለው መተካት መሆኑ ተገልጾአል:: የተሻሩትና የተተኩት አንቀጾች (ሕጎች) ብዛት በተለያዩ ሰዎች ግምት ከአምስት እስከ አምስት መቶ የሚደርስ ሲሆን፤ ብዙዎች ወደ ፪፻፳፭ ገደማ እንደሆነ ይገምታሉ:: የሱፍ አሊ የተባለ ስለዚህ የተሻሩና የተለወጡ የቁርአን አንቀጾች ሲከራከር «የሕጉ ዓይነትና ሁኔታ እንደጊዜው ፍላጎትና ሁኔታ ሊለያይ ይችላል» በማለት ሂደታዊ የሆነ መገለጥ እንደሚያስፈልግ ይገልጻል:: ሂደታዊ መገለጥ በክርስትናም ተቀባይነት ያለው ነው:: እግዚአብሔር ብሉይ ኪዳንን የሠራው በዚያን ዘመን የነበሩት እስራኤላውያን የነበሩበትን መንፈሳዊ ደረጃና ዓቅም፣ ማኅበረሰባዊና አካባቢያዊ ሁኔታዎችን ባገናዘበ መልኩ ነበር:: እንዲሁም እስከ ጊዜው አገልግሎ በመፈጸም የሚለወጡ ሕጎች ነበሩ (ለምሳሌም የኦሪቱ መሥዋዕት በሐዲስ

ኪዳን በክርስቶስ ተተክቷል):: በሐዲስ ኪዳን በክርስቶስ ለሚፈጸሙት ነገሮች ምሳሌና አመልካች ሆነው የሚያገለግሉም ነበሩ:: በሕገ ኦሪት ሞግዚትነት ሲንከባከብ ከቆየ በኋላ፤ በዘመነ ሐዲስ ደግሞ ወንጌልን ሠራ:: ሆኖም ግን የወንጌል ሕግ አስቀድሞ ከተሠራው ከብሉይ ኪዳን ጋር አይጋጭም::

በቁርአን ላይ ችግሩ የሂደታዊ መገለጥ ጉዳይ ከመሐመድ በፊት ስለተሰጡ ሕግጋት መሻሻል የሚናገር ሳይሆን፤ በራሱ በመሐመድ ዘመን ተሰጥተው እንደገና በእርሱው ዘመን የተሻሩና የተሻሻሉ ሕጎች የመኖራቸው ነገር ነው:: ሱራ ፪:፩፻፲፮፣ ፲፯:፹፮፣ ፲፮:፩፻፩:: እነዚህ ሁሉም ከመሐመድ በፊት ከብዙ ጊዜያት በፊት ስለተሰጡና አሁን በዘመናት መለ ወጥ ምክንያት መለወጥ ወይም መሻሻል ስላስፈለጋቸው ሕጎች ሳይሆን በራሱ በቁርአን ስላሉ ሕጎች መለወጥና መሻር የሚናገሩ ናቸው:: በሃያ ዓመት ውስጥ ሂደታዊ መገለጥ ትርጉሙ ምን ላይ ነው? በብሉይና በሐዲስ ኪዳን መካከል ያለው የዘመን ልዩነት ፲፮፻ ዓመት ነው:: በዚህ ጊዜ ውስጥ ብዙ ማኅበረሰባዊ ነገሮች ስለሚለወጡ ከነዚህ ለውጦች ጋር ለማስማማት ተለወጠ ቢባል፤ ለውጡ የሕዝቡን ሁኔታ ለማገናዘብ ስለሚሆን ትርጉም ይኖ ረዋል:: ነገር ግን አስቀድሞ የሰጠውን ሕግ በሃያ ዓመት ውስጥ፣ ያውም ብዙ ነገር በተ ደጋጋሚ የሚለውጥ ከሆነ አላህ ሁሉን ለማወቅ ይቸገራል ወደሚል ድምዳሜ ያመራ ናል:: ሌላው አማራጭ አሳብ የሚሆነው ደግሞ ጸሐፊው ሲጽፍ መሳሳቱን በኋላ በማወቁ ያን ለማስተካከል ሲል አንዱን መሻር ሌላውን ማሻሻል ሌላውን ደግሞ መለወጥ አስፈ ለገው:: እንግዲህ የትኛው ሊሆን እንደሚችል የራስን ግንዛቤ መውሰድ ይቻላል:: ለማንኛ ውም ከእነዚህ መሻሻሎችና መለወጦች ለአብነት ያህል የተወሰኑትን እንመልከት::

፩. በሱራ ፪:፻፵፪-፻፵፬ የጸሎት አቅጣጫ (ቂብላ) ከመካ ወደ ኢየሩሳሌም እንደገናም መልሶ ወደ መካ ሲለወጥ እናገኛለን::
፪. ውርስን በተመለከተ ሱራ ፬:፯ እና ፪:፻፹ ለሴቶችና ለወንዶች እኩል ድርሻ ይሰጣሉ:: በሱራ ፬:፲፩ ላይ ግን የወንዶቹ ድርሻ እጥፍ ሆኗል::
፫. የሌሊት ጸሎት በሱራ ፸፫:፪-፬ ሙሉውን ሌሊት እንዲሆን የታዘዘ ሲሆን በ፸፫:፳ ላይ ደግሞ ወደ ግማሽ ከዚያም በታች የሚቻለውን ያህል ወደሚል ተሻሽሎአል::
፬. ሥነ ፍጥረታት የተፈጠሩባቸው ቀናት ብዛት ከስድስት (፯:፶፬፣ ፳፭:፶፱) ወደ ስምንት ተለ ውጧል (፵፩:፱-፲፪)
፭. የነቢያት መዓርግ ለውጥ:- መጀመሪያ እኩል የነበሩ ሲሆን (፫:፹፬ ፪:፪፻፹፭ ፪:፻፴፮) በሱራ ፪:፪፻፶፫ ላይ ግን አንዳንዶቹ ከሌሎቹ በላይ ናቸው ተብሏል::
፮. የሰይፍ አንቀጾች:- *«የተከበሩትም ወሮች ባለቁ ጊዜ ጣዖት አምላኪዎችን ባገኛችኋቸው ሥፍራ ግደሉአቸው፤ ያዙአቸውም፤ ክበቡአቸውም፤ እነርሱንም ለመጠበቅ በየመንገዱ ተቀ መጡ»* ይላል:: ፱:፭:: ክርስቲያኖችንም *«ከነዚያ መጻሕፍትን ከተሰጡት ... እነርሱ የተዋ ረዱ ሆነው ግብርን በእጆቻቸው እስከሚሰጡ ድረስ ተዋጉአቸው»* (፱:፳፱) ይላል:: *«ሃይማኖትም ሁሉ ለአላህ ብቻ እስከሚሆን ድረስ ተጋደሉዋቸው»* (፰:፴፱):: *«እነዚያን የካዱትንም በጽኑ ቅጣት ቅጣቸው»* (፱:፫):: እነዚህ ሁሉ በሱራ ፪:፪፻፶፮ ላይ *«በሃይ ማኖት ማስገደድ የለም»* የተባለውን የሚቃረኑ ናቸው::
፯. ባላቸው የሞተባቸው ሴቶች በሱራ ፪:፪፻፴፬ ላይ ለአራት ወራትና አሥር ቀናት እንዲ ታገሡ ያዛል:: ሱራ ፪:፪፻፵ ላይ ግን ይህ ወደ አንድ ዓመት ተለውጧል::
፰. ለአላህ የተገዛው የመጀመሪያው ሰው መሐመድ ነው ይላል (፮:፲፬ ፩፻፷፫፣ ፴፱:፲፪):: ሆኖም እነዚህ አባባሎች ቀደም ብሎ አብርሃምና ልጆቹ እንዲሁም ያዕቆብና (፪:፻፴፪) ሌሎቹ ቀደምት ነቢያት (፳፰:፶፪-፶፫) እና ሐዋርያት ሳይቀሩ (፫:፶፪) ቀደምት ሙስሊሞች ናቸው ያለውን ዘንግቶት ነው::
፱. አላህ ሐሰተኞችን ሁሉ ይጠላል፣ ይበቀላል፤ መሐመድን ግን መሐላ እንዲያፈርስ ይፈ ቅድለታል (፷፮:፩-፪)
፲. ሱራ ፶፩:፶፮ ላይ ጂን የተፈጠረው ለአላህ ለመገዛት ነው ይላል፤ ሱራ ፯:፻፸፱ ላይ ደግሞ ጅን የተፈጠረው ለሲዖል ነው ይላል::

፲፮. በሱራ ፸፱:፴-፴፩ የኃጢአት ዝንባሌና ምኞት ተወግዟል። ሆኖም በሱራ ፬:፳፬-፳፭ ላይ አላህ ብዙ ሴቶችን ማግባትን፣ ፍቺን፣እንዲሁም ሴት ምርኮኞችንና ባሪያዎችን ቅምጥ ማድረግን ይፈቅዳል። (ቅምጥ ማስቀመጥና ብዙ ሚስቶችን ማግባት ከአመንዝራዊ ፍላጎት ውጭ ለሌላ ለምን እንደሚያገለግሉና እንደሚፈለጉ የሚያውቀው አላህ ብቻ ነው) በተጨማሪም ታማኞች ለሆኑት ከሞት በኋላ በገነት የሚያገኙት ዋጋቸው ቆንጆ የሆኑ ብዙ ሴቶችን ማግኘት ነው። ታዲያ ፍትወት በምድር ላይ የተጠላና ስሕተት ከሆነና ለቅዱስ አምላክ የማይስማማ ከሆነ በገነት እንዴት ብሎ ነው እርሱ ወዶና ፈቅዶ ሽልማት አድርጎ የሚሰጠው?

፲፯. ሙስሊሞች፣ አይሁዶች፣ ክርስቲያኖችና ሳቢያኖች ሁሉም በመጨረሻው ቀን ፍርሃት የሌለባቸውና የዳኑ ናቸው ይላል (፪:፷፪)። *«እነዚያ ያመኑ፣ እነዚያም ይሁዳውያን የኾኑ፣ ክርስቲያኖችም ሳቢያኖችም (ከነርሱ) በአላህና በመጨረሻው ያመነ መልካምንም ሥራ የሠራ ለነርሱ በጌታቸው ዘንድ ምንዳቸው አላቸው፤ በነርሱም ላይ ፍርሃት የለባቸውም፤ እነርሱም አያዝኑም።»* ሆኖም ሱራ፫:፹፭ ላይ እንደገና ሙስሊሞች ብቻ እንደሚድኑ ይናገራል። *«ከኢስላም ሌላ ሃይማኖትን የሚፈልግ ሰው ፈጽሞ እርሱ ተቀባይ የለውም፤ እርሱም በመጨረሻይቱ ቀን ዓለም ከከሳሪዎቹ ነው»* ይላል።

ምናልባት ከእነዚህና ከሌሎችም ብዙ ችግሮች መካከል የተወሰኑት ሊታገሷቸው የሚቻልና ከባድ ችግር ላይሆኑ ይችሉ ይሆናል። ነገር ግን ቁርአን ምንም ዓይነት የሰው እጅ ሳይነካውና ተጽእኖ ሳያደርግበት በቀጥታ ከሰማይ የወረደ ነው የሚለው ነገር ነው፤ እነዚህንና ሌሎች ብዙ ነገሮችን ቀርቶ አንድን ችግር እንኳ በምንም ዓይነት ቅን ሕሊና ብንሆን ለመታገሥ የሚከብድ ነው። ቁርአን ላይ ለውጦችና ማሻሻያዎች የሚደረጉ ከሆነና ቁርአን ከዚህ የተቀዳና ከሰማይ የወረደ ከሆነ (፹፭:፳፪) በሰማይ ያለው «ያልተፈጠረው» ዋናው መጽሐፍም እነዚህን ለውጦችና ሽረቶች ይዟል ማለት ነው። ታዲያ በሃያ ዓመት ጊዜ ውስጥ ይህን ያህል ለውጥ የተደረገበት ነገር እንዴት የአላህ ዘላለማዊ ቃል ነው ሊባል ይችላል?

ከዚህም ጋር እኩል የሚረብሽ የሚሆነው ነገር ደግሞ ይህ ጉዳይ በእግዚአብሔር ባሕርይ ላይ ያለው አንድምታ ነው። በቁርአን ላይ አላህ በፊት የተናገራቸውን ቃላትና የሰጣቸውን ትእዛዛት ሳይጠብቅ በየጊዜው ከበፊቱ ጋር የሚቃረንና የሚጣላ ነገር የሚናገር፤ ራሱን ደስ እንዳለውና በዘፈቀደ እንደሚያደርግ አድርጎ የሚገልጥ ከሆነ፤ መሐመድ አስቀድሞ አጸናዋለሁ ያለውን መገለጥ የሚያፈርስ ባዕድ አስተሳሰብ ይሆናል። እነዚህ መለወጦችና የሕግ ሽረቶች በሃያ ዓመት ውስጥ የተፈጠረ የማኅበረሰብ አስገዳጅ ሁኔታዎችን የሚያሳዩ ሳይሆኑ አንድን ሰውና የእርሱን ጓደኞች ፍላጎት ለአንድ የተወሰነ አካባቢና ለአንድ የተወሰነ ጊዜ የሚያገለግሉ ነበሩ።

## በቁርአን ያሉ ስሕተቶች

በቁርአን ውስጥ የተለያዩና ብዙ ስሕተቶች አሉ። እነዚህም ከታሪክ እውነታ ጋር የሚጋጩ፣ የሰዋስው ስሕተቶች፣ ትርጉም የለሽ የሆኑ ነገሮች፣ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር የሚጋጩና ከታወቁ እውነታዎችም ጋር የሚጣረሱና የማይሄዱ ናቸው። ከእነዚህ ውስጥ በአጭሩ የምናየው ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር የሚጋጩትን የተወሰኑትን ብቻ ነው።

በቁርአን ውስጥ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር የሚጋጩ ብዙ አንቀጾችና ሐተታዎች አሉ። የተወሰኑትን ከላይ ተመልክተናቸዋል፤ ስለዚህ እዚህ ላይ አንደግማቸውም። ቁርአን እነዚህም መጻሕፍት (መጽሐፍ ቅዱስን) እንደሚከተልና እነርሱን የሚያስከብር እንደሆነ ስለሚናገር (ሱራ ፮:፴፬፤ ፲:፷፬፤ ፬:፹፪) ይዘቱ አስከብራቸዋለሁ ከሚላቸው መጻሕፍት ጋር የማይስማማ ከሆነ እውነተኛነቱ ትልቅ ጥያቄ ምልክት ላይ ይወድቃል።

## ሥላሴን በተመለከተ

ቁርአን የሥላሴን እምነትና ትምህርት የገለጸው ሙሉ በሙሉ በተሳሳተ መልኩ ነው። የሱራ ፭:፻፲፮ ጸሐፊ ክርስቲያኖች ሦስት አማልክትን እንደሚያመልኩ በማስመሰል እጅግ በጣም በተሳሳተ ሁኔታ ጽፏል። እነዚህ ሦስት አማልክት የተባሉትም አብ፣ ድንግል

ማርያም እና ኢየሱስ እንደሆኑ አድርጎ ጽፏል፡፡ *«አላህም የመርየም ልጅ ዒሳ ሆይ አንተ ለሰዎቹ እኔንና እናቴን ከአላህ ሌላ ሁለት አምላኮች አድርጋችሁ ያዙ ብለሃልን? ... »* ይላል፡፡ ክርስቲያኖች ግን ቅድስት ድንግል ማርያምን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ እናት እንደ መሆኗ ተገቢውን ክብር እናከብራታለን እንጂ አምላክ ናት አንልም፡፡ አምላካችን እግዚአብሔር ብቻ ነው፡፡ እግዚአብሔር ስንልም አብ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ማለታችን ነው፡፡ ታዲያ ይህን የፈጠራ ነገር የቁርአን ጸሐፊ ከየት አመጣው? በታሪክ እንደሚነገረው ኮሎሪዲያኖች የሚባሉ ድንግል ማርያምን የሚጨምር የሦስትነት አስተሳሰብና አምልኮ የነበራቸው መናፍቃን በመሐመድ ዘመን በመካከለኛው ምሥራቅ ነበሩ፡፡ ምናልባት መሐመድ ይህንን ስህተት ከነዚህ መናፍቃን ያገኘው ሊሆን ይችላል፡፡ በዘመኑ የነበሩት ክርስቲያኖች የሚያ መልኩትን ለይቶ የማያውቅ ሰው ከሰማይ እንዲህ ያለ ነገር ተገለጠልኝ ማለቱ ይገርማል፡፡ የበለጠ የሚገርመው ግን የርሱ እንዲህ ማለት ሳይሆን የሌሎች እርሱን መከተል ነው፡፡

ከላይ እንደተገለጸው ይህንን በተመለከተ ሌላ ስሕተትም አለ፡፡ ሱራ ፭፡፸፫-፸፭ «እነዚያ አላህ የሦስት ሦስተኛ ነው የሚሉ በእርግጥ ካዱ» ይላል፡፡ ይህ ክስ በክርስቲያኖች ላይ መሆኑ ግልጽ ነው፤ ሆኖም ግን ክርስቲያኖች እግዚአብሔር ከሦስቱ አንዱ ነው ብለው አያምኑም፡፡ ይህ ዓይን ያወጣ ስሕተት ብቻ ሳይሆን የስም ማጥፋት ወንጀልም ነው፡፡ ለማሳያ እነዚህን አነሣን እንጂ ሌሎችም ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር በቀጥታ የሚጋጩ ብዙ አሉ፡፡